# ተበዳይ በዳይ ሆኖ የቀረበበት የኢጋምሳ ከተማ የንጹሃን አማሮች የጅምላ ጭፍጨፋ

*በአማራ ማህበር በአሜሪካ (Amhara Association of America) የተዘጋጀ ሪፖርት*

*መስከረም 2፥ 2015 ዓም (September 12, 2022)*

## ማውጫ


1. **መግቢያ** ........................................ 2

2. **የምርመራው ዋና ዋና ግኝቶች** ........................................ 2

3. **የምርመራ ውጤት በዝርዝር** ........................................ 3

3.1. በኢጋምሳ ከተማ በሚገኝ ካምፕ ውስጥ የነበረ የኦሮሞ ልዩ ሀይል ከከተማዋ በድንገት ለነዋሪዎች አሳሳች መረጃ በመስጠት ስለመውጣቱ... 3

3.2. የኦሮሞ ልዩ ሀይልን መውጣት እግር በእግር ተከትለው የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች ወደ ከተማዋ ስለመግባታቸው ........................................ 5

3.3. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት የኢጋምሳ ከተማን በተቆጣጠረባቸው ቀናት ውስጥ የተፈጸሙ ብሄር ተኮር ግድያዎች፣ አፈናዎች እና ሌሎች የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ........................................ 9

ሀ) ብሄር ተኮር ግድያዎች ........................................ 9

ለ) ከቁም እስርና ስቃይ በኋላ ለአደባባይ ፍርድ የቀረቡ አማራዎች ........................................ 15

3.4. በኢጋምሳ ከተማ ነሀሴ 24/2014 ዓ.ም ለረጅም ሰአት የቆየ የተኩስ ልውውጥ ስለመኖሩና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰው ህይወት ስለመጥፋቱ ........................................ 18

3.5. 'በፋኖ' ታጣቂዎች ተገደሉ የተባሉ የኦሮሞ ንጹሀን፡-ሲገድሉ ሸኔ ሲሞቱ ንጹሀን የሚሆኑት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት አባላት ........................................ 20

3.6. የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በኦሮሞ ክልል እየተፈጸመ ባለው አማራ ተኮር የዘር ፍጅት ተባባሪ ከመሆን እንዲታቀብ ስለማሳሰብ ........................................ 23

4. **ማጠቃለያ** ........................................ 26

## 1. መግቢያ

ወትሮም ቢሆን አማራ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ጭፍጨፋዎች በሰፊው ከሚፈጸሙባቸው የኦሮሞ ክልል ዞኖች ውስጥ አንዱ በሆነው በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን፣ አሙሩ ወረዳ፣ አጋምሳ ከተማ በንጹሀን ላይ ጅምላ ግድያ እንደተፈጸመ ለአማራ ማህበር በአሜሪካ መረጃ ከደረሰበት ከነሀሴ 23/2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 3/2014 ዓ.ም ድረስ ማህበሩ ተፈጸሙ ስለተባሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ባለሙያዎችን በመመደብ ምርመራ ሲያደረግ ቆይቷል፡፡ በምርመራው ሂደትም የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ሰለባዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ የዓይን እማኞችና ምስክሮችን ጨምሮ 33 ሰዎች በመረጃ ምንጭነት የተሳተፉበት ሲሆን ስለተፈጸመው ጉዳይ፣ ስለ ፈጻሚዎቹ ማንነት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የሰጡት ምልከታ በዚህ ሪፖረት በአጭሩ ቀርቧል፡፡

## 2. የምርመራው ዋና ዋና ግኝቶች

- የምርመራው ውጤት እንደሚያሳየው በኦሮሞ ክልል የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን አሙሩ ወረዳ የምትገኘውን አጋምሳ የተባለች ከተማን በጊዜያዊነት ተቆጣጥረው የነበሩት የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት (በተለምዶ "ኦነግ-ሸኔ") ታጣቂዎች ነሀሴ 23/2014 ዓ.ም በከተማዋ ውስጥ በመዘዋወር የአማራ ብሄር ተወላጆችን በመለየት በፈጸሙት ጭካኔ የተሞላበት የግድያ ተግባር ከ50 በላይ ንጹሀን አማራዎች ሲገደሉ፤ ቢያንስ 20 አማራዎች ደግሞ በታጣቂዎቹ የእገታ ተግባር ከተፈጸመባቸው በኋላ ደብዛቸው ጠፍቷል፡፡
- በእለቱ የተከፈተውን ዘር ተኮር ጥቃት ተከትሎ የሚደርስላቸው የመንግስት አካል በመጥፋቱ ጭንቀት ውስጥ የገቡ የአጋምሳ ከተማ አማራ ነዋሪዎች ባሰሙት የድረሱልን ጥሪ በአጎራባች የገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ እና አጋምሳ ከተማ ውስጥ ቤተሰብ ያላቸው የግል እና የመንግስት ታጣቂ አማራ አርሶ አደሮች ተሰባስበው በማግስቱ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) ጠዋት ወደ ከተማዋ ሲገቡ ቀድመው ተዘጋጅተው ይጠብቋቸው የነበሩ የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች፣ ብሄራቸው ኦሮሞ የሆኑ የመንግስት ሚሊሾች እና የግል ታጣቂዎች ተኩስ በመክፈታቸው በተፈጠረ ረጅም ሰአት የቆየ የተኩስ ልውውጥ ሳቢያ ከሁለቱም ወገን በርካታ ተፋላሚዎች የተገደሉ ሲሆን ከዚያ በተጨማሪ የከተማ ላይ ውጊያ በመሆኑ ሳቢያ በተባራሪ ጥይት ምክንያት ህጻናትን ጨምሮ ከ10 ያልበለጡ ያልታጠቁ ኦሮሞዎች ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል፡፡
- የነበረውን የተኩስ ልውውጥ ተከትሎ ታፍነው የነበሩትን አማሮች በከፊል ማስለቀቅ የተቻለና ከከተማዋ እንዲወጡ የተደረገ ቢሆንም የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎችና ጀሌዎች ወደ ከተማዋ በመመለስ በተለያየ ምክንያት ያልሸሹ አማራዎችንና ከአማራ ጋር የተጋቡ እንዲሁም በአንድ በኩል የአማራ ደም

ያላቸውን ለይተው ከነሀሴ 23 አመሻሽ ጀምሮ ግድያ ፈጽመዋል፡፡ይሁንና የአማራ ማህበር በአሜሪካ በዚህ ጉዳይ ላይ የጀመረውን ምርመራ ገና ስላላጠናናቀ በዚህ ሪፖርት ላይ አልተካተተም፡፡

## 3. የምርመራ ውጤት በዝርዝር

### 3.1. በአጋምሳ ከተማ በሚገኝ ካምፕ ውስጥ የነበረ የኦሮሞ ልዩ ሀይል ከከተማዋ በድንገት ለነዋሪዎች አሳሳች መረጃ በመስጠት ስለመውጣቱ

የአማራ ማህበር በአሜሪካ ያነጋገራቸው ከጥቃቱ የተረፉ የከተማዋ ነዋሪዎች እንደገለጹት ጥቃቱ የተፈጸመው አጋምሳ ከተማ  ካምፕ ውስጥ የነበሩ የኦሮሞ ልዩ ሀይሎች እሁድ ነሀሴ 22/2014 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰአት አካባቢ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ድንገት ከተማዋን ለቀው በመውጣታቸው የተፈጠረውን የጸጥታ ክፍተት በመጠቀም ነው፡፡ እንደ አይን እማኞቹ ገለጻ የኦሮሞ ልዩ ሀይል  አባላት ከተማዋን ለቀው ከመውጣታቸው ከሰአታት በፊት ሲገለገሉባቸው የነበሩ እቃዎችን ሲሰበስቡ የታዩ ሲሆን በሁኔታው የተደናገጡ የአማራ ተወላጆች  ከተማዋን ለቀው ለመሸሽ የእለት ጉርስ እና ልብሶችን በመሰብሰብ ሂደት ላይ እያሉ ከአማራው ማህበረሰብ  የተውጣጡ ግለሰቦች   ወደ ልዩ ሀይሎቹ በመሄድ ''አደጋ ላይ እንዳለን እያወቃችሁ ለሞት ትታችሁን አትሂዱ፤ ካልሆነም  እዚህ ቆይተን ከምንታረድ  አብረናችሁ እንድንወጣ ፍቀዱልን'' በማለት የተማጸኑ ቢሆንም በልዩ ሀይሉ አስተባባሪዎች በኩል የተሰጣቸው ምላሽ ''የሚሄደው ከፊሉ የልዩ ሀይል አባል እንጂ ሁሉም አይደለም፡፡ ስለዚህ ልትሰጉ አይገባም'' የሚል ነበር፡፡ የአማራ ብሄር ተወላጆችም ከልዩ ሀይሉ የተሰጣቸውን ማስተማመኛ ቃል ይዘው ቀድመው ለመሸሽ የተዘጋጁትንም ጭምር  በማረጋጋት ወደ ቤታቸው የተመለሱ ቢሆንም የልዩ ሀይሉ አስተባባሪዎች ግን ቃላቸውን አጥፈውና ጨለማን ተገን አድርገው  ሙሉ ሀይሉን ከከተማዋ ከምሽቱ አንድ ሰአት አካባቢ እንዲወጣ አድርገዋል፡፡

ቀደም ብሎ ልዩ ሀይሉ ትቷቸው እንዳይወጣ ለመማጸን ሄደው ከነበሩት ሰዎች ውስጥ አንዱ የነበረው እና ከጥቃቱ እንደምንም ሸሽቶ ወደ አጎራባች ቀበሌ እንደገባ የሚናገረው በ 30ዎቹ እድሜ ክልል የሚገኝ ወጣት የነበረውን ሁኔታ ለ አማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ሲገልጽ፡-

> ''የሆነብን ነገር ሁሉ ያሳዝናል፡፡ ላለፉት አመታት ተወልደን ባደግንበት ከተማ ውስጥ በተፈጸሙብን ጥቃቶች ብዙዎች የቅርብ ቤተሰቦቻችንን ህይወት በግፍ ተቀምተናል፤ የቀረነውም ''ከሞቱት በላይ በህይወት ካሉት በታች'' ሆነን ተሳቀን እና አንገታችንን ደፍተን መቆየታችን አልበቃ ብሎ ሸኔ እንደሚጨርሰን እየታወቀ እሁድ ከሰአት በኋላ የልዩ ሀይሉ

አባላት ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ሲጠቀሙባቸው የቆዩ መገልገያዎቻቸውን መሸከፍ ጀመሩ፡፡ ይህን የተመለከተው የ አማራ ማህበረሰብ በመደናገጥ የቻለውን ይዞ ለመሸሽ መሯሯጥ ጀመረ፡፡ ይህን ጊዜ እኔ እና ጓደኞቼ ሽማግሌዎችን በማነጋገር ልዩ ሀይሉ ወደ ሚገኝበት ካምፕ ሄደን እግራቸው ላይ ወድቀን ''ለሞት ጥላችሁን አትሂዱ፡፡ መሄዳችሁ የግድ ከሆነም የጸጥታ ሽፋን ስጡን እና ከዚህ አካባቢ ወጥተን በብዛት የአማራ ተወላጆች ወደሚገኙበት የገጠር ቀበሌዎች እንድንገባ አግዙን'' ስንል ለመናቸው፡፡ የሰጡን ምላሽ ሽኔ እንዳለ እያወቅን እንዴት ትተናችሁ እንወጣለን፡፡ የሚወጣው ከፊሉ ሀይል ሲሆን ከፊሉ እናንተን እየጠበቀ እዚሁ ይቆያል የሚል ነው፡፡ "

በወቅቱ ልዩ ሀይሉ የሰጠውን ምላሽ በመተማመን አብረውኝ የነበሩ ጓደኞቼ እና ሽማግሌዎቹ ወደ ነዋሪው በመመለስ ከተማውን ለቆ ለመውጣት ሲሯሯጥ የነበረውን ወገናችንን በማረጋጋት ወደቤት እንዲመለስ የማድረግ ስራ መስራት የጀመሩ ቢሆንም "ከዚህ በፊት የሆነውን ስለማውቅ የሚፈጠረው አይታወቅም በሚል ሮጠው ማምለጥ የማይችሉ አቅማቸው የደከሙ አረጋውያንን በከፊል ይሄዳል ካሉት የልዩ ሀይል አባል ጋር ይዘውልን እንዲሄዱ ጠየኳቸው" የሚለው የመረጃ ምንጫችን ''ምንም ችግር የለም፤ መውጫ መንገድ ላይ ጠብቀን ይዘናቸው እንሄዳለን፤'' እንደተባለ ነገር ግን ቃላቸውን ማጠፋቸውን በምሬት ይናገራል፡፡

"ቀድሞም ቢሆን እኛን ለመጠበቅ የሚቀሩ የልዩ ሀይል አባላት እንደሚኖሩ ሲነገረን ከዚህ በፊት የደረሰብንን ስለማውቅ ለማመን ተቸግሬ ነበር፡፡ ቢያንስ ግን ሮጠው ማምለጥ የማይችሉ አንድ አምስት የሚሆኑ አረጋውያንን ይዘውልን እንደሚወጡ የገቡልኝን ቃል አይፈጽሙም የሚል ጥርጣሬ አልነበረኝም ነበር፡፡ በመሆኑም ገና በቀኑ አረጋውያኑን ይዤ ልዩ ሀይሉ በሚወጣበት መንገድ ላይ ቁጭ ብዬ መጠበቅ ጀመርኩ፡፡ ሆኖም ይወጣሉ ከተባሉበት ሰአት በኋላ እንኳን ለሰአታት ብንጠብቅም ሊመጡ አልቻሉም፡፡ እንደዚያም ሆኖ ምን ገጥሟቸው ይሆን እያልኩ ከማሰብ ውጪ በተስፋ መጠባበቄን አላቆምኩም ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ በግምት ከምሽቱ አንድ ሰአት በኋላ ሙሉ በሙሉ በመጨለሙ ምክንያት በአይኔ ባይታየኝም ከከተማው የሚወጣ የመኪና ድምጽ እኛ ወዳለንበት አቅጣጫ ሲመጣ ሰማሁ፡፡ በፍጥነት የእጅ ባትሪዬን አብርቼ የልዩ ሀይል መኪኖች መሆናቸውን ካረጋገጥኩ በኋላ ቃል በገቡልኝ መሰረት ሽማግሌዎቹን ይዘውልኝ እንዲሄዱ እንዲያቆሙልኝ በባትሪዬ በመታገዝ ምልክት ሰጠኋቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም የልዩ ሀይል ተሽከርካሪዎች ምንም ምላሽ ሳይሰጡኝ ተከታትለው አልፈውኝ ሄዱ፡፡ በጣም የሚያሳዝነው እኔ እንደሆንኩ እና ሽማግሌዎቹን ይዘውልን እንዲሄዱ በተነጋገርነው መሰረት እየጠበኳቸው እንደሆነ በደንብ አውቀውታል፡፡ ለዚህም ማሳያው በዚያ በጨለማ አሳቻ መንገድ ላይ እንኳን ባትሪ አብርቶባቸው ይቅርእናዝም ብሎ መንገድ ላይ የተገኘን ሰው ካለው የጸጥታ ስጋት አኳያ ዝም ብለው አያልፉም ነበረ፡፡ያን ቀን ግን እኔ መሆኔን ስላወቁ የተሽከርካሪያቸውን መብራት እንኳን ሳያበሩ ነው እኔ እና ሽማግሌዎቹን አልፈውን የሄዱት፡፡ ይሄ ግልጽ ነው ታርደን እንድናልቅ ፈርደውብን ነው፡፡ መጀመሪያውንም ቢሆን ጨለማ ተገን አድርገው እና የተሽከርካሪዎቹን መብራት ሳያበሩ የወጡበት ዋነኛው ምክንያት ህዝቡ ቃል ከገቡት በተቃራኒ ሙሉ በሙሉ ጠቅለው ሲወጡ እዳያያቸው ነው፡፡"

በተመሳሳይ የአማራ ማህበር በአሜሪካ ያነጋገራቸው ሌሎች አምስት ከጥቃቱ የተረፉ እና ሁለት በጥቃቱ ሳቢያ የቤተሰብ አባሎቻቸውን ያጡ የከተማዋ ነዋሪዎች እንደገለጹት ልዩ ሀይሉ ትቶን መውጣቱ ሳያንስ ከተማዋ ውስጥ የሚቀሩ የልዩ ሀይል አባላት አሉ እነሱ ይጠብቋችኋል በሚል የውሸት ቃል በመስጠት ህዝቡ አስቀድሞ እንዳይሸሽ በማድረግ ለእልቂት ዳርገውታል ሲሉ የልዩ ሀይል አባላቱን ኮንነዋል፡፡ የአማራ ማህበር በአሜሪካ እንዳረጋገጠው ሁሉ ቀደም ብለው በጉዳዩ ላይ ዘገባ የሰሩ የሚዲያ ተቋማትም ሆነ መረጃ ያጋሩ ሌሎች አካላት (የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንን ጨምሮ[1]) የኦሮሞ ልዩ ሀይል አባላት  እሁድ ነሀሴ 22/2014 ዓ.ም አመሻሽ ላይ ከኢጋምሳ ከተማ ለቀው እንደወጡ አረጋግጠዋል፡፡[2] ነገርግን ከዚህ በታች ባለው የሪፖርቱ ክፍል በስፋት እንደተቀመጠው ቀደም ብለው በደረሰው ጭፍጨፋ ዙሪያ የዘገቡ አብዛኞቹ ሚዲያዎችም ሆነ ሌሎች አካላት ''የጥቃቱን ፈጻሚዎች እና የጥቃቱን ሰለባዎች'' በተመለከተ ያስተላለፉት መረጃ  ከእውነት የራቀ እና መሬት ላይ ያለውን እውነት ያላገናዘበ እንደሆነ የአማራ ማህበር በአሜሪካ  ያካሄደው ምርመራ ያሳያል ፡፡

## 3.2. የኦሮሞ ልዩ ሀይልን መውጣት እግር በእግር ተከትለው የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች ወደ ከተማዋ ስለመግባታቸው

የአማራ ማህበር በአሜሪካ ያነጋገራቸው ሁሉም የመረጃ ምንጮች በአንድ ድምጽ እንደገለጹት በከተማዋ የነበረው የኦሮሞ ልዩ ሀይል ''ለአማራ ነዋሪዎች የሰጠውን መተማመኛ ቃል'' በመሻር ጨለማን ተገን አድርጎ እና የአሽከርካሪዎቹን መብራት አጥፍቶ ሙሉ በሙሉ  መውጣቱን ከሰሙበት አንድ  ሰአት ባልሞላ የቆይታ ጊዜ ውስጥ  ተደጋጋሚ የጥይት ድምጽ በመስማታቸው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎች ወደ ከተማዋ እንደገቡ ጥርጣሬ እንዳደረባቸው ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆን የቻሉት ግን ጠዋት ከእንቅልፋቸው ሲነሱ እራሳቸውን ከበባ ውስጥ ወድቀው ካገኙ በኋላ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከጥቃቱ ሸሽተው ወደ ምስራቅ

[1] https://ehrc.org/%e1%8a%a6%e1%88%ae%e1%88%9a%e1%8b%ab-%e1%8a%ad%e1%88%8d%e1%88%8d%e1%8d%a1-%e1%89%a0%e1%88%86%e1%88%ae-%e1%8c%89%e1%8b%b1%e1%88%a9-%e1%8b%88%e1%88%88%e1%8c%8b-%e1%8b%9e%e1%8a%95-%e1%8a%a1%e1%88%99/

[2] DW  'የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን አሙሩ ወረዳ ግጭት ያስነሳው ውዝግብ' ‹https://www.dw.com/am/የሆሮ-ጉዱሩ-ወለጋ-ዞን-አሙሩ-ወረዳ-ግጭት-ያስነሳው-ውዝግብ/a-63011085›. BBC NEWS አማርኛ 'በኦሮሞ ሆሩ ጉዱሩ ወለጋ በርካታ ሰላማዊ ሰዎች በታጣቂዎች መገደላቸው ተነገረ' ‹https://www.bbc.com/amharic/articles/cnk8xj09k3eo› .

ወለጋ ዞን ወደሚገኝ አጎራባች ቀበሌ ከገቡ በሙቶዎች የሚቆጠሩ የአጋምሳ ተፈናቃዮች ውስጥ አንዱ እንደሆነ እና በ 20ዎቹ የእድሜ ክልል ላይ እንደሚገኝ የተናገረ ወጣት ሁኔታውን በሚከተለው መልኩ ገልጾታል፡-

> ‘’ልዩ ሀይሉ የወጣበት እና የሸኔ ታጣቂዎች ወደ ከተማው የገቡበትን ሰአት ስንመለከት ‘እየወጣን ስለሆነ እናንተ ግቡ‘ ያሏቸው ነው የሚመስለው፡፡ ልዩ ሄይሉ እንደወጣ በሰማን ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች የጥይት ድምጽ መሰማት ጀመረ፡፡ ሸኔዎች ስለመሆናቸው አልተጠራጠርኩም፡፡ በመሆኑም ህይወቴን ለማትረፍ ቤት ውስጥ ከመቀመጥ ቤተክርስቲያን ብሄድ የተሻለ ነው ብዬ ስላሰብኩ አጋምሳ ከተማ ወዳለ የስላሴ ቤ/ር ሄጄ እዛው አደርኩ፡፡ ነገርግን በሸኔዎች እጅ ላይ ከመውደቅ አላመለጥኩም፡፡ ጠዋት ላይ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በመግባት ጫካው ውስጥ የነበሩ ሁለት አዛውንት አገልጋዮችን ከገደሉ በኋላ ቤተመቅደስ ውስጥ ተደብቀን የነበርነውን ስድስት አካባቢ የምንሆን አማራዎች ደግሞ በቁጥጥር ስር አዋሉን፡፡”

የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች መሆናቸውን በምን አወቅክ ተብሎ በመርማሪዎች ለተነሳለት ጥያቄ ‘’ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ብሄር ተኮር ጥቃቶችን ስለፈጸሙብን ሸኔዎችን ለመለየት ለእኛ አያስቸግረንም፡፡ ረጃጅም ሹርባ የተሰራ ጸጉር ያላቸው.፣ ጺማቸው በጣም ያደገ፣ ዩኒፎርም የለበሱ እና ኦሮሚኛ ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው፡፡ ከዚያ በተጨማሪ ት/ቤት ውስጥ ሰብስበውን “የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት’’ እንደሆኑ እና ከዚህ በኋላ መንግስት እንደሆኑ በግልጽ ነግረውናል’’ ሲል ገልጿል፡፡

በተመሳሳይ እድሜዋ 35 አካባቢ እንደሆነና በአጋምሳ ከተማ ጫፍ ላይ በሚገኝ ጎዶማሮ በተባለ ጎጥ ነዋሪ እንደነበረች የምትናገረው የሶስት ልጆች እናት በተፈጠረው ችግር ምክንያት ወደ ሀሮ ቀበሌ ተፈናቅላ የገባች መሆኑን በማንሳት የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች ከተማውን ይዘው እንደነበረ እና ይህንንም በአይኗ እንዳየች በዚህ መልኩ ገልጻዋለች፡-

> “ልዩ ሀይሉ እሁድ ምሽት ላይ ከተማውን ጥሎ ከወጣ በኋላ በማግስቱ ጠዋት ስንነሳ በ ሸኔ ቁጥጥር ስር ሆነናል[…]. ከፍተኛ ጭፈራ እና የተኩስ ድምጽ ነበር፡፡ ይገሉናል ብዬ ስለፈራሁ ከሶስት ልጆቼ (ሁለቱ የ 3 እና የ 5 አመት ህጻናት ነበሩ) ጋር በመሆን በሬን ዘግቼ ተቀመጥኩ፡፡ ልክ አንድ ሰአት አካባቢ ሲሆን የከተማው ነዋሪ የሆነና ከዚህ በፊት የማውቀው አለማየሁ የተባለ ኦሮሞ ከሌላ ከማላውቀው አንድ ሰው ጋር መጥቶ ‘’ነይ ውጪና ከእነልጆችሽ አዲሱን መንግስትን ተዋወቂ ’’ በማለት ከቤቴ አስወጥተውን እየገፈታተሩ ወደዋናው የከተማው ክፍል ወሰዱን፡፡ ከዚያ ሸኔዎች በአንድ ላይ ሰብስበው ይጠብቋቸው ወደነበሩ በቁጥር 20 የሚደርሱ ሌሎች እንደኛው ከየቤታቸው የተሰበሰቡ አማራ ነዋሪዎች ጋር ቀላቀሉን፡፡”

በተመሳሳይ ከየቤታቸው ተሰብስበው በተለያዩ ቦታዎች በቁም እስር ላይ ከነበሩት አማራዎች መካከል አጋምሳ ከተማ 03 ቀበሌ ባለ ባዶ ቤት ውስጥ ከ7 አማራዎች [ሚስቱንና ልጁን ጨምሮ] ጋር ታግቶ አንደነበረ የሚናገረው እድሜው 30ዎቹ መጀመሪያ ላይ የሆነ ወጣት ሸኔዎች አጋምሳ ከተማን ከ ነሀሴ 22 ምሽት ጀምሮ እንደተቆጣጠሩና እሱን ጨምሮ ብዙ አማራዎች በቁም እስር ላይ እንደነበሩ በዚህ መልኩ ያስታውሰዋል፡-

> “እኔ የምኖረው 03 ቀበሌ ከባለቤቴእናአንድ ልጄ ጋር ነው፡፡ እሁድ ማታ ልዩ ሀይሉ ሲወጣ ሸኔዎች ገብተው አደሩ፡፡ ሰኞ (ነሃሴ 23) ጠዋት ስንነሳ ሙሉ ከተማው አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ነበር፡፡ ከተማው በሸኔ ቁጥጥር ስር በመሆኑ የተደሰቱ ቄሮዎች [ኦሮሞ የሆኑ የአካባቢው ወጣቶች] ወደ አደባባይ በመውጣት ከታጣቂዎቹ ጋር በመሆን እየጨፈሩ እና እየተኮሱ በከተማዋ ውስጥ ያሉ ባንኮችን እና የንግድ ሱቆችን እየዘረፉ እና አይንውሀቸው ያልወደደውን አማራ እየገደሉ ሌሎችን ደግሞ እያፈኑ ነበር፡፡ ሁኔታው አስፈሪ ቢሆንም ከከተማዋ የሚያሶጡት መንገዶች በሙሉ በሸኔ ታጣቂዎች እንደተዘጉ መረጃው ስለነበረኝና ልጄንና ባለቤቴን ይዤ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማምለጥ እንደማልችል ስለገባኝ የነበረኝ ብቸኛው አማራጭ ሁሉንም ለፈጣሪ ሰጥቼ የሚመጣውን ከባለቤቴእናልጄ ጋር ቤት ቁጭ ብሎ መጠበቅ ነበር፡፡ ሁለት ሰአት አካባቢ ሲሆን በቁጥር ከ 10 የማይበልጡ የሸኔ ታጣቂዎችእናአብረውኝ ያደጉ ብዙ ቄሮዎች ወደቤታችን መጥተው ሁላችንም እንድንወጣ ካደረጉ በኋላ ቤት ውስጥ ያገኙትን ሁሉ ዘረፉ፡፡ በመቀጠል በኤሌክትሪክ ሽቦ እየገረፉን ከቤታችን ትንሽ ራቅ ብሎ ወዳለ ባዶ ቤት (የግለሰብ ይመስለኛል) በመውሰድ ከእኛ በፊት ታፍነው ከነበሩ 5 አማራዎች -በኋላ ላይ ሲነግሩኝ ሁሉም የአንድ ቤተሰብ አባላቶች ናቸው-ጋር ቀላቀሉን፡፡”

እንደሌሎቹ የመረጃ ምንጮች ሁሉ ከተማዋን የወረሯት የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች (ሸኔዎች) እንደሆኑ እንደማይጠራጠር የገለጸው ወጣቱ ታጣቂዎቹ የሚናገሩት ቋንቋ ኦሮሚኛ መሆኑ፣ ጸጉራቸው ሸኔዎች እንደሚያደርጉት ሹርባ የተሰራ መሆኑ፣ ጫካ ላይ የከረሙ ስለመሆናቸው የሚያሳየው የአለባበስ እና የንጽህና ሁኔታቸው፣ ከተማዋ ላይ ከገቡ በኋላ አማራን እየመረጡ ሲገድሉ ወይም ሲያፍኑ በተቃራኒው ቄሮዎችን ባንኮችንና የአማራ ሱቆችን ማዘረፋቸውን በምክንያትነት አንስቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ታጣቂዎቹ ራሳቸው በተደጋጋሚ የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት እንደሆኑና ‘’ኦሮሞን ነጻ አውጥተው በቁጥጥራቸው ስር እንዳደረጉ’’ ሲናገሩ እደነበር አስታውሷል፡፡

በአጋምሳ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ስላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ እንደነበሩ የሚናገሩት የ68 አመት አዛውንት በበኩላቸው ሰኞ (ነሃሴ 23) ማለዳ ከቤታቸው ‘’ሸኔዎች’’ ባሏቸው ታጣቂዎች በኤሌክትሪክ ገመድ እየተገረፉ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ኢትዮ ቴሌ መስራያ ቤት አጠገብ ከሚገኘው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ግቢ እንደወሰዷቸውና ‘’ኦሮሞ እና የኦሮሚያ ነጻ ወጥተዋል፤ የአማራ እጣፋንታ በህዝብ ይወሰናል’’ ሲሉ

እንደሰሟቸው ተናግረዋል፡፡ እንደመታደል ሆኖ ከልጆቻቸው ጋር በህይወት ከከተማዋ መውጣት እንደቻሉ የሚናገሩት አዛውንቱ “ቀናቸው የደረሰ አማራዎች’’ ሲሉ የጠቀሷቸው ብዙዎች ግን ህይወታቸውን በአሰቃቂ ሁኔታ እንዳጡና ቁጥራቸው በወል የማይታወቁ ደግሞ ደብዛቸው እንደጠፉ ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ ሌሎች በኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎችና በቄሮዎች የቁም እስረኛ ተደርገው እንደነበሩና በዚህ ሰአት ከአጋምሳ በጥቂት ኪሎሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ሀሮ ቀበሌ ተፈናቅለው እንደሚገኙ የገለጹ ስድስት የመረጃ ምንጮች ከላይ በዝርዝር የተገለጹትን የምስክርነት ቃሎች በማጠናከር የአጋምሳ ከተማ ከነሀሴ 22 ማታ ጀምሮ በኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ታጣቂዎች እንደተያዘችና ቁጥራቸው በውል ያልተለየ አማራዎች ሲገደሉና ደብዛቸው ሲጠፉ እነሱ እንደመታደል ሆኖ በህይወት ከአጋምሳ ከተማ ሸሽተው መውጣት እንደቻሉ ተናግረዋል፡፡

ከላይ በዚህ ሪፖረት በዝርዝር እንደተመለከተው  የኦሮሞ ልዩ ሀይል ከአጋምሳ መውጣቱን ተከትሎ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ወደከተማዋ መግባቱን ቀደም ብለው የወጡ ጥቂት የማይባሉ የመገናኛ ብዙሀን  በጨረፍታም ቢሆን አመልክተዋል፡፡[3] ነገርግን ከዚህ በታች በዝርዝር  እንደተመለከተው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎችና በአጋምሳ ከተማ የሚገኙ ‘’ቄሮዎች’’ ሲሉ የአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ያነጋገሯቸው የመረጃ ምንጮች የጠቀሷቸው የከተማዋ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሞ ወጣቶች ከሰኞ (ነሃሴ 23) ጠዋት ጀምረው በከተማዋ የተለያዩ ክፍሎች ተበታትነው እየጨፈሩ ቤት ለቤት በመዞር ‘’አማራ በመሆናቸው ብቻ’ የጨፈጨፏቸውን አዛውንቶች፣ ሴቶች እና ህጻናትን ጨምሮ ከ 61 በላይ የሚደርሱ ንጹሀንን እንዲሁም ከየቤቱ በአማራነታቸው ተለይተው በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ ባዶ ቤቶች ውስጥ ስልካቸው ተቀምቶ ከታፈኑ በኋላ ‘የእናንተ እጣፋንታ የሚወሰነው በኦሮሞ ህዝብ ነው በሚል’  ሲገረፉና ሌሎች አካላዊና ስነልቦናዊ በደል ለሰአታት ሲያደርሱባቸው የነበሩ በርካታ ንጹሀንን በተመለከተ ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ አድርገው በዝምታ ማለፋቸውን የሚያሳዝን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

---

[3] DW  ‘የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን አሙሩ ወረዳ ግጭት ያስነሳው ውዝግብ’ ‹https://www.dw.com/am/የሆሮ-ጉዱሩ-ወለጋ-ዞን-አሙሩ-ወረዳ-ግጭት-ያስነሳው-ውዝግብ/a-63011085›.
BBC NEWS አማርኛ ‘በኦሮሞ ሆሩ ጉዱሩ ወለጋ በርካታ ሰላማዊ ሰዎች በታጣቂዎች መገደላቸው ተነገረ’ ‹https://www.bbc.com/amharic/articles/cnk8xj09k3eo› .

## 3.3. የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት የአጋምሳ ከተማን በተቆጣጠረባቸው ቀናት ውስጥ የተፈጸሙ ብሄር ተኮር ግድያዎች፣ አፈናዎች እና ሌሎች የሰብአዊ መብት ጥሰቶች

### *ሀ) ብሄር ተኮር ግድያዎች*

የኦሮሞ ነጻነት ሀይል ታጣቂዎቹ ወደ አጋምሳ ከተማ መግባት ተከትሎ የኦሮሞ ወጣቶች' (እንደምንጮች አገላለፀ "ቄሮዎች") እጅግ ደስተኞች እንደነበሩና ይህንንም በተለያዩ የከተማዋ አቅጣጫዎች እየተዘዋወሩ በጭፈራና በሆታ ሲገልጹ እንደነበረ፤ በመቀጠል ደግሞ ከታጣቂዎቹ ጋር በከተማዋ እየተዘዋወሩ ባንኮችንና ንብረትነታቸው የአማራ የሆኑ ንግድ ቤቶችን ከመዝረፍ ጀምሮ 'በአማራ ተወላጆች' ላይ ያነጣጠረውን ግድያና አፈና በግንባር ቀደምትነት ሲመሩ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡ በተቃራኒው የአማራው ማህበረሰብ ከዚህ በፊት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎች በህጻናትና ሴቶች ላይ ሳይቀር ሲፈጽሙት የነበረውን ብሄር ተኮር ጅምላ ጭፍጨፋ ስለሚያውቁና የእነሱም እጣፋንታ ከዚያ የዘለለ እንደማይሆን ስላሰቡ ቀኑን ከምድረ ገጽ የሚጠፉበት የምጽአት ቀናቸው አድርገው ተቀብለውት እንደነበር በመገረም ያስታውሱታል፡፡

ከአጋምሳ ተፈናቅሎ አጎራባች ወደ ሆነው ጃቦ ደቦን ቀበሌ የተቀመጠ በ20ዎቹ የእድሜ ክልል መጨረሻ ላይ የሚገኝ ወጣት በጥቃቱ ሳቢያ አባቱ ኪሊሸር ተብሎ በሚታወቅ ሰፈር ባለው ቤታቸው እንደተገደለበትና በአጠቃላይ ሰኞ (ነሃሴ 23) እለት የነበረውን ሁኔታ እንዲህ ይገልጸዋል፡-

> *"የሆነው ሁሉ ያሳዝናል፡፡ በእለቱ ከሸኔዎች ጋር በማበር ቄሮዎች እና የመንግስት ታጣቂ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች በደስታ እየጨፈሩ ያገኙትን አማራ ሲገሉ ሲያፍኑ እንዲሁም ንብረት ሲያወድሙ ነበር፡፡ ጥቃቱ የተከፈተው ከከተማዋ የሚያስወጡ መንገዶችን በመዝጋት ስለነበር አምልጦ መውጣት አስቸጋሪ ሆነ፡፡ ስለሆነም ገሚሶቻችን በቆሎ ማሳ ውስጥ ገብተን ተደበቅን፡፡ ሌሎች ደግሞ ጫካ ውስጥ ገቡ፡፡በአቅራቢያው የሚደበቅበት ነገር የሌለው ደግሞ ቤቱ ቁጭ ብሎ ሞቱን መጠባበቅ ግዴታው ሆነ፡፡ የእኔ አባት በወቅቱ ኪሊሸር የሚገኘው ቤታችንን እጠብቃለሁ በሚል በግቢያችን ውስጥ ከአንድ ጓደኛው ጋር ነበር፡፡ ከቀኑ ስድስት አካባቢ ሲሆን ከአባቴ ጋር የሚተዋወቅ ብሄሩ ኦሮሞ የሆነ ደረጀ ሽፈራው የሚባል የመንግስት ታጣቂ ከሌሎች ኦሮሞ ታጣቂዎች ጋር ወደ ቤታችን እንደመጡና አባቴም ''የመንግስት ታጣቂዎች መሆናቸውን'' ስለሚያውቅና ይገሉኛል የሚል እምነት ስላልነበረው ለምን እንደፈለጉት ሊጠይቃቸው ሲጠጋ ደረቱን መተው እንደገደሉት ከአባቴ ጋር አብሮ የነበረውና እሱንም ሊገድሉት ሲተኩሱ ያመለጠ ጓደኛው ነገረኝ፡፡ ሁኔታው እጅግ አስፈሪ የነበረ ቢሆንም ከወንድሞቼ ጋር በመሆን የአባቴን ሬሳ አስነስቼ ስላሴ ቤተክርስቲያን አቅራቢያ ያለ ጫካ በጥድፊያ ቀብረን ወደ በቆሎ ማሳ ውስጥ ተመልሰን ገባን፡፡"*

ከአባቱ በተጨማሪ ብዛት ያላቸው የአማራ ተወላጆች በካራና በጥይት እንደተገደሉና ሌሎች ደግሞ ከየቤታቸው ተለቅመው በተለያዩ ቦታዎች በቁም እስር ላይ ተይዘው እንደነበረ ይናገራል፡-

"በዋነኛነት የሸኔ ታጣቂዎችና ቄሮዎች አልፎ አልፎ ደግሞ ብሄራቸው ኦሮሞ የሆኑ የመንግስት ታጣቂዎች በከተማዋ እየተዘዋወሩ ደስያላቸውን እየገደሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ አባቴን ለመቅበር ከበቆሎ ማሳ ውስጥ በወጣሁበት ቅጽፊት ኪሊሽር የምትባል ሰፈር ላይ ብቻ ልንገረው ጋሻዬ፣ ቻሌ ጌታሁን፣ ባዬህ ጀንበሩ፣ መለስ፣ መንጌ እና ባምላኩ የሚባሉትን ጨምሮ ከ10 በላይ አማራዎች ተገድለው አይቻለሁ፡፡"

ከሟቾቹ መካከል ልንገረው ጋሻዬ የተባለው በ40ዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኝ በሙያው ግንበኛ የነበረ ሰው እደሆነ በመጥቀስ 01 ቀበሌ (ኪሊሽር ሰፈር) አስፓልት ላይ አንገቱን በካራ ቆርጠው እንደገደሉት ተናግሯል፡፡ በተመሳሳይ ቻሌ ጌታነህ የተባለው እድሜው በግምት ሰላሳዎቹ መጨረሻ ላይ የነበረ 'ጭቃ መራጊ' እና መንጌ (በግምት እድሜው 45 አመት የሆነ የከብት እረኛ) አንገታቸው በካራ ተቆርጦ አንዳየ የገለጸ ሲሆን ባዬው ጀንበሩ (የቀን ሰራተኛ) እና መለስ (የቀን ሰራተኛ) ደግሞ በጥይት ተመተው መሞታቸውን ለ አማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ገልጻል፡፡ በየቦታው ሰው እየታረደ እንደነበረና ለረጅም ሰአት ምንም አይነት የመንግስት ሀይል ሊታደጋቸው እንዳልቻለ የሚናገረው ግለሱቡ በመጨረሻ በአጎራባች ቀበሌ የሚገኙ ዘመዶቻቸው እንዲደርሱላቸው ጥሪ ማድረጋቸውን ገልጹዋል፡፡

እድሜዋን በትክክል እንደማታውቀው ነገር ግን 30 አካባቢ እንደምትሆን የምትናገረው ሌላዋ የመረጃ ምንጭ በበኩሏ ''ጸጉራቸውን ሹርባ የተሰሩ'' ስትል የገለጸቻቸው ታጣቂዎች ሰኞ (ነሃሴ 23) ጠዋት አንድ ሰአት አካባቢ ሲሆን ኢጋምሳ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አካባቢ በሚገኘውና ከባለቤቷ ጋር ወደምትኖበት ቤት በመምጣት የትዳር አጋሯ የሆነውን ቻሌ ጌታሁንን ከቤት በማውጣት የበራቸው ጎበን ላይ አጋድመው በእሷና በ 5 አመት ልጇ ፊት ጭካኔ በተሞላበት መልኩ አርደው እንደገደሉት ለ አማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች እያለቀሰች አስረድታለች፡-

"ሰኞ (ነሃሴ 23) ጠዋት አንድ ሰአት አካባቢ ነው፡፡ እኔ፣ ባለቤቴ እና የ5 አመት ልጃችን (ሀብታም ቻሌ) ቤታችንን ተቀምጠን ነበር፡፡ ከየት እንደመጡ የማላውቃቸው ጸጉራቸውን ሹርባ የተሰሩ ታጣቂዎች መጡ፡፡ ከዚያ እሱን ከቤት ውስጥ ጎትተው አውጥተው እኔ እና ልጃችን እያየን በሩ ላይ አስደግፈው በካራ አረዱት፡፡"

ከዚያ በኋላ ምን እንደተፈጠረ እንደማታስታውስ የገለጸችው ተበዳዩዋ ከሰአታት በኋላ እራሷን ጫካ ውስጥ እንዳገኘችውና ሂወቷን ለማትረፍ ወደ ሆሮ ቀበሌ በእግሯ ተጉዛ ከምሽቱ ሁለት ሰአት አካባቢ እንደደረሰች ገልጻለች፡፡ የልጇን (ሀብታም ቻሌ) ሁኔታ በተመለከተ ትሙት ትኑር እንደማታውቅና አባቷን ሲያርዱት እያየች እንደነበረች ብቻ እንደምታስታውስ በጸጸት ተናግራለች፡፡

የአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ያነጋገሩት ሌላው የመረጃ ምንጭ ወጣትና የቤተክርስቲያን መምህር ሲሆን በአጋምሳ ከተማ በሚገኘው ስላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከጥቃቱ ለማምለጥ ተሸሽጎ በነበረበት ጊዜ 'አነግ ሸኔ' ያላቸው ታጣቂዎች በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመግባት መሪጌታ ይታይህ አለምነህ የተባሉ እድሜያቸው በ80ዎቹ የሚገመት አገልጋይንና እማሆይ ቸኮለች በዛብህ የተባሉ (በግምት 65 አካባቢ) የቤተክርስቲያኑን አቃቢ በጥይት ደብድበው ሲገሏቸው እንዳየ ይገልጻል፡፡

> "ሸኔ ከተማውን እሁድ ማታ እንደተቆጣጠረ ስሰማ ለደህንነቴ የተሻለ ነው በሚል ወዲያውኑ ስላሴ ቤተክርስቲያን ሄድኩ፡፡ አዳሬንም መቅደሱ ውስጥ ገብቼ ከሌሎች እንደኔው በስጋት ከመጡ ጋር አደረኩ፡፡ ከነጋ በኋላም እንኳን ድንገት ቢመጡና ግቢ ውስጥ ካገኙን ይገድሉናል ብለን ስላሰብን ከመቅደሱ አልወጣንም፡፡ እማሆይ ቸኮለችና መሪጌታ ይታይህ ግን ብሄራቸው አማራ ቢሆንም ሽማግሌዎች ስለሆንን አይነኩንም ብለው ስላሰቡ ግቢ ውስጥ እደወትሮው አንዳንድ ነገሮችን ከኦሮሞ አገልጋዮች ጋር በመሆን እየሰሩ ነበር፡፡ በግምት 1 ሰአት አካባቢ እንግዳ የሚመስል ድምጽ ሰምቼ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ በቤተክርስቲያኑ ግንብ ላይ ባሉ ጥቃቅን ቀዳዳዎች አጮልቄ በምመለከትበት ቅጽበት ሸኔዎች እማሆይ ቸኮለችና መሪጌታ ይታይህን ተኩሰው  ገደሏቸው፡፡ በመቀጠል ቤተመቅደስ ውስጥ ያለነውን ስድስት የምንሆን ሰዎችን አውጥተው ሊገሉን ሲሉ በቤተክርስቲያኗ ቅጥር ግቢ ውስጥ የነበሩና ብሄራቸው ኦሮሞ የሆኑ አባቶች መሀል ገብተው ''በመጀመሪያ እኛን ግደሉን፤ ከዚያ እነሱን ትገድላላችሁ'' በማለታቸው እዚያው ከመገደል ተረፍን፡፡ ነገርግን እንደ ሌላው አማራ ሁሉ የእኛም እጣ ፈንታ ቴሌ አጠገብ ባለው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በሚደረግ ስብሰባ በኦሮሞ ህዝብ እንደሚወሰን ተነግሮን በጎማ እየገረፉ ይዘውን በመሄድ በመቶዎች ከሚቆጠሩ አማራዎች ጋር ቀላቀሉን፡፡"

የመሪጌታ ይታይህ አለምነህና የእማሆይ ቸኮለች በዛብህን አስከሬን ታጣቂዎቹ ከቤተክርስቲያኗ ቅጥር ግቢ አንስተው በመውሰድ በ100 ሜትሮች ርቀት ላይ በሚገኝ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን አካባቢ እንደቀበሯቸው የቤተክርስቲያን መምህሩ ገልጸዋል፡፡

ከአጋምሳ ከተማ ሸሽቶ በአሙሩ ወረዳ ስር በምትገኘው ጃቦ ደበን ቀበሌ የሚገኝ ወጣት በበኩሉ በተለያዩ የከተማው ክፍሎች በአጠቃላይ ከ50 በላይ የሚሆኑ አማሮች እንደተገደሉና ከ20 በላይ የሚሆኑትን መዝገቦ እንደያዘ ይናገራል፡፡

> "ከቤታቸው ከታገቱ በኋላ ደብዛቸው የጠፋውን ሳይጨምር ከ50 በላይ አማራዎች ተገለዋል፡፡ እኔ በግሌ በአካል የማውቃቸው የነበሩና በጥቃቱ ሳቢያ መገደላቸውን ያረጋገጥኳቸው ሰዎች አሉ፡፡ በምሳሌነት ብጠቅስልህ መብራቱ ብርሌው (በ60ዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኝ)፣ ጓዴ በየነ (40ዎቹ የእድሜ ክልል የነበረና በካራ የታረደ) ፣ አስማረ በልስቲ (40ዎቹ የእድሜ ክልል የነበረ) ፣ በቃሉ ማስረሻ (40ዎቹ የእድሜ ክልል የነበረ የቀን ሰራተኛ)፣ ጥሌ ጌትነት (እዚሁ

አጋምሳ ተወልዶ ያደገ ወጣት)፣ እማሆይ ቸኮለች በዛብህ (የስላሴ ቤተክርስቲያን አገልጋይ)፣ መሪጌታ ይታይህ አለምነህ (የስላሴ ቤተክርስቲያን አገልጋይ)፣መንጌ የሚባል በ50ዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኝ ጎልማሳ እማ ጸሀይ ከምትባል ባለቤቱ ጋር ፣ሌሎች ሶስት ተቀጥረው ከብት የሚያግዱ የነበሩ ድንቁ፣ ፈለቀ እና አባ ቀሬ የተባሉ ምስኪኖች፣ባምላኩ ሽፈራው፡፡ እነኝህ እኔ ቀድሜ የማውቃቸውና በጥቃቱ መገደላቸውን ያረጋገጥኳቸው ብቻ ናቸው፡፡ ከአጋምሳ ከተማ በምሸሸበት ጊዜ በየቦታው አንገታቸው ታርደው ወይም በጥይት ተመተው የወደቁ ብዙ ስማቸውን የማላውቀው ሰዎች ነበሩ፡፡”

በአጋምሳ በደረሰው ጥቃት ባምላኩ ሽፈራው የተባለ የቅርብ ዘመዳቸው በምሳርና በድንጋይ ተደብድቦ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበትና በቃሬዛ ወደ ሀሮ ቀበሌ እንዲመጣ ቢደረግም ህክምና ባለመኖሩ ሳቢያ ህይወቱ እንዳለፈ የሚናገሩት ደግሞ ነዋሪነታቸውን ሀሮ ቀበሌ ላይ ያደረጉ አዛውንት ናቸው፡፡

“ሰኞ (ነሃሴ 23) ጠዋት በሸኔ እንደተከበቡና ህይወታቸው አደጋ ላይ እንደወደቀ ነገረን፡፡ አንደፈራው አልቀረም ቤቱ ገብተው በምሳርና በድንጋይ እንዳይሆን አደረጉት ብለው አመጡልኝ፡፡ ልጆቹና ባለቤቱስ ብዬ ብጠይቅ ባለቤቱን እንደገደሏት እንዲሁም ከ 6 ልጆቹ አንዷን አላየናትም እንጂ ሌሎቹም ታርደው በወደቁበት አይተናል አሉኝ፡፡ እንግዲህ ምን ልበል? ለማን አቤት ይባላል? እሱም ቢሆን እዚህ ሲደርስ ነፍስያው በጣም ደክማ ነበር፤ ሰውነቱም በደም ተጨማልቋል፡፡ ምን አይነት ጭካኔ እንደሆነ እንጃ ብቻ ጆሮውን ሳይቀር ቆርጠውታል፡፡ እማደርገው ጥፍት አለኝ፡፡ሀኪም አይባል ህክምና አገልግሎት እኛ ጋር የለም፡፡ እኛም ዙሪያውን ተከበን ከሀኪም አገልግሎት ከራቅን ሁለት አመት ሞላን፡፡ እንዲሁ ስባትት ምንም ሳላደርግለት ህይወቱ አለፈ፡፡ በማግስቱ ሀሮ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አስቀብሬ ይሄው ሀዘን ተቀምጨያለሁ፡፡”

የአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ያነጋገሯቸው የተለያዩ የመረጃ ምንጮች የሰጡትን ቃል መሰረት በጭፍጨፋዉ ቢያንስ 61 አማራዎች እንደተገደሉ ያረጋገጠ ሲሆን ስም ዝርዝራቸው እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

<u>**የተገደሉ አማራዎች ዝርዝር**</u>

| ተ.ቁ | የሟች ስም | እድሜ | ጾታ |
|---|---|---|---|
| 1 | መሪጌታ ይታይህ አለምነህ | 80ዎቹ የሚገመት | ወ |
| 2 | እማሆይ ቸኮለች በዛብህ | 65 አካባቢ የሚገመት | ሴ |
| 3 | ባምላክ (ባምሌ) ሽፈራው | 50 | ወ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | መብራቱ ብርሌው | 60 | ወ |
| 5 | ልንገረው ጋሻዬ (ግንበኛ) | 38 | ወ |
| 6 | ቻሌ ጌታነህ (ጭቃ መራጊ) | 36 | ወ |
| 7 | ምሳዋ ካሳው | 30ዎቹ የምትገመት | ሴ |
| 8 | ፈቀደ (የምሳዋ ልጅ) | ህጻን | ወ |
| 9 | ሻንቆ (የምሳዋ ልጅ) | ህጻን | ወ |
| 10 | በለጥ ካሳው (የምሳዋ እህት) | - | ሴ |
| 11 | ጓዴ በየነ | 41 | ወ |
| 12 | ብርሀኑ ጌትነት | 32 | ወ |
| 13 | ጥሌ ጌትነት | 27 | ወ |
| 14 | ጌትነት ተገኝ | 60 | ወ |
| 15 | በቃሉ ማስረሻ (የቀን ሰራተኛ) | 50ዎቹ የሚገመት | ወ |
| 16 | ሲሳይ አዲሱ | 34 | ወ |
| 17 | ዘላለም ይርኮ (በአንድ በኩል ኦሮሞ) | 28 | ወ |
| 18 | አታላይ መለሰ | 37 | |
| 19 | ወንዴ (የቀን ሰራተኛ) | - | ወ |
| 20 | እማ ሞሲት (የወንዴ ባለቤት) | - | ሴ |
| 21 | ሚጣ ወንዴ (ልጃቸው) | ህጻን | ሴ |
| 22 | ጌጡ ወንዴ (ልጃቸው) | ህጻን | ወ |
| 23 | አስማገረ በልስቲ | 40 | ወ |
| 24 | ባንቺ አሰፋ (እናት) | 38 | ሴ |
| 25 | አዳነ ባምላኩ (ልጅ) | 19 | ወ |
| 26 | ርስቱ ባምላኩ (ልጅ) | 15 | ወ |
| 27 | አለኸኝ ባምላኩ (ልጅ) | 12 | ወ |
| 28 | ሀሰን ይመር (የኦቦራ ነዋሪ የነበረ) | - | ወ |
| 29 | ምትኩ(የኦቦራ ነዋሪ የነበረእናጋሪ የሚነዳ) | - | ወ |
| 30 | ጌታሰው ስጦታው | 32 | ወ |
| 31 | አለምነው መኮንን | 40 | ወ |
| 32 | አብዩ ካስዩ | 19 | ወ |
| 33 | አላምር ታረቀኝ | 33 | ወ |
| 34 | አባ ፈለቀ (እረኛ) | 70ዎቹ የሚገመቱ | ወ |
| 35 | ንጉስ ዳኛው[4] | 30ዎቹ የሚገመት | ወ |

[4] ንጉስ ፈንታው በሚል የገለጹት ሁለት የመረጃ ምንጮች ነበሩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 36 | አባ ቀሬ (ከብት እረኛ) | ከ60 በላይ | ወ |
| 37 | አለ በላይ | - | ወ |
| 38 | ባይህ አንማው | 37 | ወ |
| 39 | ድንቁ እንደሻው | 50 | ወ |
| 40 | መለስ ካሳሁን | 27 | ወ |
| 41 | መለስ እንደሻው | 30ዎቹ መጀመሪያ | ወ |
| 42 | እማሆይ ጸሀይ | 60ዎቹ የምትገመት | ሴ |
| 43 | መንጌ ባምላኩ[5] | - | ወ |
| 44 | አየነው እንደሻው | 30 | ወ |
| 45 | ፈንታው ታመነ | 51 | ወ |
| 46 | አዳነ መኮንን | 40 | ወ |
| 47 | ጸጋ አስማረ | 42 | ሴ |
| 48 | አሌ ስማቸው | 35 | ወ |
| 49 | ታሪኬ ሰማሀኝ | 25 | ሴ |
| 50 | ማርከሽ ጋሻው | ከ 30 በላይ | ወ |
| 51 | ብርሀኑ እርገጤ | ከ 25 በላይ | ወ |
| 52 | ክንዴነው ወርቁ | ከ 30 በላይ | ወ |
| 53 | ወንድምነው ጥላሁን | ከ 30 በላይ | ወ |
| 54 | ካሳሁን ደሳለው | ከ 30 በላይ | ወ |
| 55 | ፋንቴ አበባው | ከ 25 በላይ | ወ |
| 56 | ሲሳይ ፈረደ | ከ 30 በላይ | ወ |
| 57 | ሞላ ብርቁ | ከ 30 በላይ | ወ |
| 58 | ሙላት አስናቀው | ከ 30 በላይ | ወ |
| 59 | ጀንበሩ ታከለኝ | ከ 30 በላይ | ወ |
| 60 | ግርማ (አባት ያልተረጋገጠ) | | ወ |
| 61 | ሀይሌ (አባት ያልተረጋገጠ) | | ወ |

[5] "መንጌ" የተባለ የአባቱን ስም የማውቁት እረኛ እንደተገደለ ሁለት የአማራ ማህበር በአሜሪካ ምንጮች የገለጹ ሲሆን ከ "መንጌ ባምላኩ" ተጨማሪ ይሁን አይሁን ለጊዜው ማረጋገጥ አልተቻለም።

## ለ) ከቁም እስርና ሲቃይ በኋላ ለአደባባይ ፍርድ የቀረቡ አማራዎች

የአማራ ማህበር በአሜሪካ ምርመራ እንዳረጋገጠው ከተገደሉት ባሻገር በእለቱ (ሰኞ (ነሃሴ 23)) በመቶዎች የሚቆጠሩ አማሮች ከቤታቸው፣ ከቤተክርስቲያንና ከተገኙበት ሌሎች ቦታዎች ተይዘው በተለያዩ ቦታዎች ለሰአታት በቁም እስር ላይ እንዲቆዩ እንደተደረገና ከፊሎቹ ከብዙ እንግልት በኋላ ሲለቀቁ ከፊሎቹ ደግሞ የደረሱበት አልታወቀም፡፡ በቁም እስር ላይ እንደነበሩና ቆይተው እንደተለቀቁ የሚናገሩ ተበዳዮች ከአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ጋር በነበራቸው ቃለመጠይቅ እንደገለጹት በወቅቱ ከደረሰባቸው ጅምላ ብሄርተኮር ስድቦች፣ እንግልትና ድብደባ ባሻገር ይገድሉናል በሚል ከፍተኛ የስነልቦና ጭንቀት ውስጥ እንደነበሩ ያስታውሳሉ፡፡

የአጋምሳ ስላሴ አገልጋይ የነበሩት የ68 አመት አዛውንት የነበረውን ሁኔታ ሲያስረዱ፡-

> "እኔን እና ሁለት ልጆቼን ቤታችን በተቀመጥንበት ነበር የያዙን፡፡ ምን አጠፋን፤ ምን በደልን ብዬ ብማጸናቸውም እየገፈታተሩንና በጎማ እየገረፉን ቴሌው [ኢትዮ ቴሌኮም መስሪያቤት] አካባቢ ካለ ት/ቤት ወሰዱን፡፡ ለሰአታት እናንተ ቆሻሾች እያሉ ሲያንገላቱንና አልፎ አልፎም በጎማ ሲገርፉን ከቆዩ በኋላ የአማራ እጣፋንታ በኦሮሞ ህዝብ ይወሰናል ብለው ለሸንጎ አቀረቡን፡፡ በስብሰባው ላይ የነበሩት የአካባቢው ወጣቶች እያዩን ሲገላምጡንና ሲሰድቡን ስለነበር በህይወት እንተርፋለን የሚል ግምት አልነበረንም፡፡ በመሆኑም ለፈጣሪ የወደድከውን አድርግ፤አንተ ታውቃለህ ብዬ የሚሆነውን መጠበቅ ጀመርኩ፡፡"

በመቀጠል 'የሸኔዎቹ መሪ' በሚል አዛውንቱ የገለጹት ግለሰብ ''ኦሮሞ እና የኦሮሚያ ነጻ ወጥተዋል'' እነዚህን [በቁም እስር ላይ የነበሩትን አማሮች] ምን ብናደርጋቸው ይሻላል ሲል ለኦሮሞ ነዋሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት እንደጠየቀና ይህን ተከትሎ እንድንሞት በሚፈልጉ ወጣቶችና ምን በደሉ በሚሉ አባቶች መካከል የሀሳብ መለያየት እንደነበረ በመጨረሻ ግን የፈጣሪ እርዳታ ተጨምሮበት እንደተለቀቁ ገልጸዋል፡፡

እድሜዋ 35 አካባቢ እንደሆነና ከሶስት ልጆቿ ጋር ለአደባባዩ ፍርድ ከቀረቡት መካከል እንደነበረች የምትናገረው እናት በበኩሏ ሰኞ (ነሃሴ 23) ጠዋት አንድ ሰአት አካባቢ ሲሆን አለማየሁ የሚባል ኦሮሞ ከዚህ በፊት ከማታውቃቸው ሰዎች ጋር ቤቷ ድረስ በመምጣት ''ነይ ውጪና ከእነልጆችሽ አዲሱን መንግስት ተዋወቂ'' በማለት እያንገላቱ እንደወሰዷትና ተቻለ ወላኔ ሆቴል አጠገብ መንገድ ላይ ከሰበሰቧቸው 20

የሚደርሱ አማሮች ጋር እንደቀላቀሏት ገልጻለች፡፡ መንገድ ላይ በቁም እስር ላይ በቆዩበት በመቀጠል ደግሞ ወደ ት/ቤት ተወስደው የነበረውን የአደባባይ ፍርድ በዚህ መልኩ አስቀምጣዋለች፡፡

“ተቻለ ወላኔ ሆቴል አጠገብ ያለው ዋና መንገድ ላይ ተቀምጠን ሳለን ሲሰድቡንና ሲገርፉን ነበር፡፡ ታጣቂዎቹ እናንተ አህዮች፤ ቆሻሾች እያሉ በወፍራም የሙብራት ጎማ [የኤሌክትሪክ ገመድ] ሲደበድቡን፤ ከተማዋ ውስጥ እየተዘዋወሩ ይጨፍሩ የነበሩ ቄሮዎች ደግሞ አማራ ከዚህ በኋላ ቀን የለሽም በባዶ እግርሽ እንደመጣሽ በባዶ እግርሽ ጎጃም ትገቢያለሽ (ምናምን ምናምን) እያሉ እየተመላለሱ ይረግጡናል፤ በድንጋይ ይሙቱናል፡፡ የቄሮዎቹ ዱላ ሲበዛብን ጠባቂዎቹ ተቻለ ወላኔ ሆቴል ስር ያለ የግለሰብ ቤት አስገቡን፡፡ ከዚያ 7 ሰአት ወይ 8 ሰአት ሲሆን ትምህርት ቤት ወስደውን ምን እናድርጋቸው ብለው የእነሱን [የኦሮሞ] ህዝብ ጠየቋቸው፡፡ ቄሮዎቹ አንድንገደል ፈልገው የነበረ ቢሆንም በእድሜ ጠና ያሉት እንድንለቀቅ ሀሳብ በማቅረባቸው ተለቀቅን፡፡”

በመለቀቃቸው ቄሮዎች [የኦሮሞ ወጣቶች]ና አንዳንዶቹ ሸኔዎች ደስተኛ እንዳልነበሩ የምትናገረው የሶስት ልጆች እናት ከተለቀቀች በኋላ ቤቷ ድረስ መጥተው እንዳይገሏት በመስጋት ከ ጎረቤቶቿ ዘንድ በመሄድ እንዳደረችና በማግስቱ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) ወደ ሀሮ እንደሸሸች ለአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች አስረድታለች፡፡

“ትምህርት ቤት ውስጥ የነበርነው ስንለቀቅ ቄሮዎችና አንዳንድ ሸኔዎች ተበሳጭተው ሲጮሁ ነበረ፡፡ ከትምህርት ቤት ስንወጣም ከኋላችን እየተከተሉ ሲያስፈራሩንና ሲሰድቡን ነበር፡፡ ቆይተው ደግሞ ቄሮዎች እኛ ስንሞት ንብረታችንን ለመውሰድ ይሁን ወይም የግል ጸብ ያላቸውን ሰው ለማጥቃት አላውቅም በየሰፈሩ በቡድን በቡድን ሆነው አንድ ወይም ሁለት ሸኔዎችን በማስከተል እንቅስቃሴያችንን ይከታተሉ ጀመር፡፡ ቤቴ ባድር ማታ መጥተው እኔንም ልጆቼንም ይገድሉናል ብዬ ስለሰጋሁ ጎረቤቴ ከሆኑ የኦሮሞዎች ቤት ዘንድ አድሬ ጠዋት ወደ ሀሮ ሸሸሁ፡፡”

በፍርድ አደባባይ ከቀረበ በኋላ ቢለቀቅም በከተማው የተለያዩ ቦታዎች አማራ ተኮር ግድያ፣ አፈና እና ዘረፋ ቀጥሎ ስለነበረ የራሱንና የቤተሰቡን ህይወት ለማዳን ጨለማን ተገን አድርጎ በቅርብ ርቀት ላይ ወደምትገኘው ጃቦደበን ቀበሌ እንደሸሸ የሚናገረው የኢጋምሳ ከተማ ቀበሌ 3 ነዋሪና እድሜው በ30ዎቹ መጀመሪያ ላይ ያለ ወጣት በበኩሉ ሁኔታውን በዚህ መልኩ ያስታውሰዋል፡-

“እኔ፣ ሚስቴና ልጄ ታፍነን በነበርንበት ባዶ ቤት ውስጥ ከእኛ ውጪ 5 የአንድ ቤተሰብ አባላት ነበሩ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት እስከሚወስዱን ድረስ እየተፈራረቁ በኤሌክትሪክ ሽቦ ሲገርፉን ነበር፡፡ ‘’ይሄ ሀገር የኦሮሞ ነው፤ ከአማራ ጋር መኖር ስለማንፈልግ ወደመጣችሁበት አልሄድ ካላችሁ ዋጋችሁን እንሰጣችኋለን፤ ከቆሻሻ ጋር አንኖርም’’ የሚሉና ሌሎች አስጸያፊ ስድቦችን ሲሰድቡን ምራቃቸውንም ሲተፉብን ነበር፡፡”

ከብዙ መንገላታት በኋላ ለፍርድ ቀርበው ቢለቀቁም ጥቃቱ ቤት ለቤት በመቀጠሉ ባለቤቱንና ልጁን ይዞ ወደ አጎራባች ቀበሌ ለመሸሽ እንደተገደደ ወጣቱ ይናገራል፡፡

> "ለጊዜው ብንለቀቅም ግድያው፣ ዘረፋው፣ አፈናው፣ስድብና ማስፈራሪያው አልቆመም ነበር፡፡ ቤቴ መጥተው ልጄን እና ሚስቴን ሲገሉ ከማይ ለመሸሽ ሞክረን ቢያንስ ብንሞት ይሻላል በሚል ወስኜ በጓደኛዬ [በአንድ በኩል አማራ በሌላ በኩል ኦሮሞ] እገዛ ጭለማውን ተገን አድርገን ከከተማዋ በመውጣት እግዚያብሄር የተመሰገነ ይሁን ጃቦ ደበን ቀበሌ እንገኛለን፡፡"

'አትሙቺ ያላት ነብስ' ሆና በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ ከሞት አመለጥኩ ሲል የ26 አመቱ የቤተክርስቲያን መምህር ይገልጻል፡፡

> "ሁሉንም ሳስብ ህልም ነው የሚመስለኝ፡፡ ጠዋት ላይ ስላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲይዙኝ አበቃልኝ ብዬ ነበር፡፡ ምክንያቱም አለም በቃኝ ብለው እግዚያብሄርን በማገልገል ይኖሩ የነበሩትን እማሆይ ቸኮለችና መሪጌታ ይታይህን ለመግደል ያላመነቱ እጆች እኔንና መሰል ወጣቶች ላይ ከመነሳት ይቦዝናሉ ብለህ ልታስብ አትችልም፡፡ ግን ፈጣሪ እንድንቆይ ስለፈለገ እዛው ሳይገድሉን በኦሮሞ ህዝብ ፊት ለፍርድ ትቀርባላችሁ ብለው ትምህርት ቤት ይዘውን ሄዱ፡፡ 8 ሰአት ገደማ ሲሆን ይገደሉ ወይስ ይለቀቁ በሚል ተከራክረው በመጨረሻ ፈጣሪ ፈቀደና ተለቀቅን፡፡"

የአማራ ማህበር በአሜሪካ ምርመራ እንደሚያሳየው ሰኞ (ነሃሴ 23) ከጠዋት ጀምሮ ከየቤታቸው እየተለቀሙ ከታፈኑ በኋላ የአማራን እጣፋንታ ለመወሰን በሚል በትምህርት ቤት ውስጥ በተካሄደው የአደባባይ ፍርድ ውስጥ ባለመቅረባቸው ያልተለቀቁ በርካታ አማሮች ደብዛቸው ጠፍቶ ቀርቷል፡፡ ከእነዚህ የደረሱበት ካልታወቁ ሰዎች ውስጥ የ20ዎቹን ማንነት በዚህ ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተካቷል፡፡

**<u>የደረሱበት ያልታወቀ ዝርዝር</u>**

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | ጾታ | እድኔ |
|---|---|---|---|
| 1 | ምስጌ ሰማኘ | ወ | 39 |
| 2 | ፈጠን (አባት ያልተረጋገጠ) | ሴ | 31 |
| 3 | ሸዋዬ ምስጌ | ሴ | 18 |
| 4 | ሙሉ ምስጌ | ሴ | 13 |
| 5 | አቡዬ ምስጌ | ወ | 8 |
| 6 | ደጉ (አባት ያልተረጋገጠ) | ወ | 31 |
| 7 | ሀብታም ሀሰን | ሴ | 25 |
| 8 | ቡርቴ ደጉ | ሴ | 13 |
| 9 | ለካ ደጉ | ሴ | 8 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | አቢ ደጉ | ወ | 6 |
| 11 | ሚጣ ደጉ | ሴ | 4 |
| 12 | ዘውዱ ደሞዝ | ወ | 41 |
| 13 | ተስፋዬ<br>(አባት ያልተረጋገጠ) | ሴ | 32 |
| 14 | አገኘው<br>(አባት ያልተረጋገጠ) | ሴ | 35 |
| 15 | መስቲ አየነው | ሴ | 18 |
| 16 | በልስቲ አየነው | ወ | 16 |
| 17 | በለጡ አየነው | ሴ | 13 |
| 18 | ሚጣ አየነው | ሴ | 10 |
| 19 | አብዲ አየነው | ወ | 7 |
| 20 | መሰረት ባምሌ | ሴ | 17 |

### 3.4. በአጋምሳ ከተማ ነሀሴ 24/2014 ዓ.ም ለረጅም ሰአት የቆየ የተኩስ ልውውጥ ስለመኖሩና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰው ህይወት ስለመጥፋቱ

የአማራ ማህበር በአሜሪካ ይህን ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ስለ አጋምሳው ጥቃት ያወጡት መረጃ መሬት ላይ የሆነውን እውነት ያላገናዘበና የኦሮሞ ብሄርተኞች ሆንብለው የፈጠሩትን ምናባዊ ትርክት የተከተለ እንደሆነ በምርመራው ያረጋገጠ ሲሆን እውነታውን በደንብ ሳይመረምሩ በተደጋጋሚ ለዘር ጭፍጨፋ እየተዳረገ ያለውን የአማራ ህዝብ ለተጨማሪ እልቂት የሚዳርግ የተዛባ መረጃ ማቅረባቸው እጅጉን አሳዝኖታል፡፡

በመገናኛ ብዙሀኑ ተዛብተው ከቀረቡት መረጃዎች አንዱ ‘’ፋኖ’’ ነሀሴ 23/2014 ዓ.ም ማለዳ ወደ አጋምሳ ከተማ ዘልቆ በመግባት በፈጸመው ግድያ ከ 60 በላይ ኦሮሞዎች ተገደሉ የሚሉ ይገኝበታል፡፡[6] ምንም እንኳን የአማራ ማህበር በአሜሪካ በተለያዩ የምእራብ ኦሮሞ ዞኖች የሚደርሱ ጭፍጨፋዎችን በመመርመር የዳበረ ልምድ ያለው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ አማራው ላይ የተፈጸሙ ብሄር ተኮር ጭፍጨፋዎችን አድበስብሶ

[6] https://ehrc.org/%e1%8a%a6%e1%88%ae%e1%88%9a%e1%8b%ab-%e1%8a%ad%e1%88%8d%e1%88%8d%e1%8d%a1-%e1%89%a0%e1%88%86%e1%88%ae-%e1%8c%89%e1%8b%b1%e1%88%a9-%e1%8b%88%e1%88%88%e1%8c%8b-%e1%8b%9e%e1%8a%95-%e1%8a%a1%e1%88%99/

ለማለፍና ተጨማሪ ጭፍጨፋ ለመፈጸም የተጎጂዎችን ስብእና ጥላሸት መቀባት እንዲሁም የተዛባ መረጃ መስጠት አማራውን ከኦሮሞ ክልል እናጸዳለን በሚል ለተያዘው ዋና እቅድ በኦሮሞ ብሄርተኞች፣ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትና በክልሉ መንግስት ሳይቀር እንደ አንድ የትግበራ ስልት ሲጠቀሙበት እንደነበረ ስለሚያውቅና ስለአጋምሳው ጭፍጨፋም የተነዙት ምናባዊ ትርክቶች የዚያ ስልት ተቀጽላ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጥርጣሬ ባይኖረውም በዚህ ደረጃ ትልልቅ መገናኛ ብዙሀንን ሳይቀር የዚህ ሴራ ወጥመድ ውስጥ መግባት ስላሳሰበው ተጨማሪ ማጣራትን አድርጎ እውነቱን ለማውጣት ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

የምርመራው ውጤትም እንደሚያሳየው ሰኞ (ነሃሴ 23) ማለዳ ጀምሮ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትና በአካባቢው የኦሮሞ ወጣቶች አማካኝነት ሲፈጸሙ የነበሩ ዘር ተኮር ግድያዎች፣ አፈናዎች እና ዘረፋዎችን ለማስቆም ምንም አይነት የመንግስት አካል ጣልቃ አለመግባቱን ተከትሎ በአጣብቂኝ ውስጥ የነበሩ የአማራ ተወላጆች በአጎራባች ቀበሌ ላሉ ቤተሰቦቻቸው የድረሱልን ጥሪ ማሰማታቸውንና ይህንንም ተከትሎ በአጎራባች ቀበሌ የሚገኙ ሽማግሌዎች በአማራው ነዋሪ ላይ የሚፈጽሙትን ግድያ እንዲያቆሙና ከከተማው በሰላም እንዲያስወጧቸው ጥሪ ቢያደርጉም እኛ በምናስተዳድረው ከተማ የፈለገንን ብናደርግ ማንም አያገባውም፤ ልብ ካላችሁ ደግሞ መጥታችሁ አስለቅቋቸው የሚል ምላሽ ከቀኑ 6 ሰአት ገደማ ከኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በኩል ተሰጥቷል፡፡ ይሁንና ወደ አጎራባች ከተማ ሄዶ ለማስለቀቅ መሞከር ቀድሞውንም በማንነታቸው ምክንያት ለሚጠሉንና እንድናልቅ ለሚፈልጉ የአካባቢው የመንግስት ሹማምንቶች የአማራውን ማህበረሰብ ለመጨፍጨፍና ለማስጨፍጨፍ ምክንያት መፍጠር ነው በሚል ሽማግሌዎች 'ቤተሰቦቻችንን ሲያልቁ አናይም፤ አጋምሳ ሄደን አብረን ብንሞት ይሻለናል' በማለት የተነሱ የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎችን እንዲረጋጉ አድርገው በድጋሚ 11 ሰአት ገደማ ለታጣቂዎቹ ግድያውን እንዲያቆሙ እና የአማራ ተወላጆች ከከተማው በሰላም እንዲወጡ እንዲፈቅዱላቸው ጥሪ እንዳደረጉ ነገርግን ጥሩ ምላሽ እንዳልገጠማቸው ይባስ ብሎ ቄሮዎችና ታጣቂዎቹ በቡድን በቡድን በመደራጀት ቀደም ሲል በኦሮሞ ሽማግሌዎች ልመና ለአደባባይ ፍርድ ቀርበው የተለቀቁ አማራዎች የሚገኙባቸው ሰፈር በመሄድ ስልካቸውን መቀማትና እንዳይሸሹ ማድረግ መጀመራቸውን የአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ያነጋገሯቸው የአይን እማኞችና ተበዳዮች ገልጸዋል፡፡ ይህን ተከትሎ አጋምሳ ከተማ ላይ ቤተሰብ ያላቸው የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎች የመንግስትና የግል ታጣቂ አማራ ገበሬዎችን በማስተባበር ወደ አጋምሳ ከተማ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) ጠዋት ላይ ጉዞ እንደጀመሩና ከተማዋ መግቢያ ላይ ሲደርሱ ተዘጋጅተው ይጠብቁ በነበሩ ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት አባላትና የአጋምሳ ከተማ የኦሮሞ ታጣቂዎች ተኩስ በመክፈታቸው ሳቢያ ቢያንስ ለ6 ሰአት የቆየ የተኩስ ልውውጥ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሳቢያ ከሁለቱም ወገኖች ብዛት ያላቸው ተፋላሚዎች የሞቱ ሲሆን በተባራሪ ጥይት ተመተው ህይወታቸው ያለፉ ጥቂት ግለሰቦች

መኖራቸውንም ምርመራው አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከነበረው የተኩስ ልውውጥ ጋር በተያያዘ በከተማዋ የሚኖሩ የሁለቱም ብሄር ተወላጆች ለህይወታቸው በመስጋት ከከተማዋ ወደ አጎራባች ቀበሌዎች ሊሸሹ ችለዋል፡፡

የአማራ ማህበር በአሜሪካ ያነጋገሯቸው የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገለጹት ሲደረግ የነበረው የተኩስ ልውውጥ ከቀኑ 8 ሰአት አካባቢ ሲሆን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትና አብረዋቸው ሲዋጉ የነበሩ የኦሮሞ ታጣቂዎች መሸሻቸውን ተከትሎ እንደቆመና አብዛኞቹ ታፍነው የነበሩት የአማራ ተወላጆች ከከተማው መውጣት ሲችሉ ጥቂት የማይባሉት ግን ደብዛቸው እንደጠፋ ቀርተዋል፡፡

መሬት ላይ ያለው እውነታ ይህ ሆኖ ሳለ በጉዳዩ ላይ ዘገባ የሰሩ ሁሉም የመገናኛ ብዙሀን ከ 6 ሰአት በላይ የቆየ የተኩስ ልውውጥ እንደነበር እንኳን ለመጥቀስ አልደፈሩም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሆን ተብሎ ተበዳዩን አካል በዳይ አድርገው ሲነዙ የነበሩ የተቀነባበሩ መረጃዎችንና ለዚሁ አላማ የተዘጋጁ የውሸት ምስክሮችን ተገቢውን ምርመራ ሳያደርጉ ዋቢ በማድረግ ፋኖ ሲሉ የገለጹዋቸውን የአማራ ገበሬዎችን ለንጹሀን ሞትና ንብረት ውድመት ተጠያቂ አድርጎ የሚያቀርብ ዘገባን ሰርተዋል።

## 3.5. 'በፋኖ' ታጣቂዎች ተገደሉ የተባሉ የኦሮሞ ንጹሀን፡-ሲገድሉ ሸኔ ሲሞቱ ንጹሀን የሚሆኑት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት አባላት

አንዳንድ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ከአማራ ክልል የኦሮሞን ድንበር ጥሰው ገቡ[7] ሌሎች ደግሞ ከአጎራባች ቀበሌዎች መጡ ባሏቸው ፋኖዎች በኦሮሞ ንጹሀን ላይ ግድያ መፈጸሙን የገለጹ ሲሆን የአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች ያነጋገሯቸው የአይን እማኞችና የአካባቢው ነዋሪዎች በበኩላቸው ይህ ሆን ተብሎ እኛን በድጋሚ ለማጥቃት የተደረገ ነው ይላሉ፡፡

ጎረቤቶቹ ሲገደሉ እሱና ባለቤቱ ደግሞ ሸኔዎች ሲል በገለጻቸው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎች በቤታቸው ታፍነው እንደነበረ የሚናገረው የ25 አመት ወጣት እለተ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) በነበረው የተኩስ ልውውጥ

[7] https://ehrc.org/%e1%8a%a6%e1%88%ae%e1%88%9a%e1%8b%ab-%e1%8a%ad%e1%88%8d%e1%88%8d%e1%8d%a1-%e1%89%a0%e1%88%86%e1%88%ae-%e1%8c%89%e1%8b%b1%e1%88%a9-%e1%8b%88%e1%88%88%e1%8c%8b-%e1%8b%9e%e1%8a%95-%e1%8a%a1%e1%88%99/

ወቅት ከተገደሉ ተዋጊዎችና በተባራሪ ጥይት ህይወታቸው ካለፈ ስድስት የሚሆኑ ንጹሀኖች ውጪ የተገደለ ኦሮሞ እንደማያውቅ ይናገራል፡፡

> "ሰኞ (ነሃሴ 23) አማራውን ሲገድሉ፣ ሲያፍኑና ሲዘርፉ አመሹ፡፡ እኔና ባለቤቴም በእለቱ ስልካችን ተቀምቶ ከቤታችን እንዳንወጣ ከታፈኑት ውስጥ ነበርን፡፡ ቀድመው በቆሎ ማሳ ውስጥ በመሸሻጋቸው ስልካቸው ያልተወሰደባቸው ወንድሞቻችን በአቅራቢያ ቀበሌዎች ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችን ባሰሙት የድረሱልን ጥሪ በማግስቱ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) ማለዳ ከተለያዩ ቀበሌዎች ተውጣጥተው እኛን ለማዳን መጡ፡፡ መጀመሪያውኑ እንደሚመጡ ሸኔዎች መረጃው ነበራቸው መሰል እኛንም እንዲጠብቁ የተመደቡትንም ጨምሮ የአጋምሳ የመንግስት ታጣቂዎችን አስተባብረው ከተማው መግቢያ ላይ ጠብቀው በከፈቱት ተኩስ ቢያንስ ለ 7 ሰአት የቆየ ፍልሚያ ተካሄዶ ሸኔዎችና ግበረአበሮቻቸው በማፈግፈጋቸው ከአፈና ማምለጥ ቻልን፡፡ እኔ እስካየሁት ድረስ በተኩሱ ልውውጡ ወቅት እኛን ለማዳን ከመጡትም እንዲሁም ከሸኔዎቹ እና አብረዋቸው ሲዋጉ ከነበሩ ታጣቂዎችም ብዙ ነብስ ጠፍቷል፡፡ በተባራሪ ጥይት ደግሞ ስድስት ያልታጠቁ ኦሮሞዎች (እኔ በስም የማውቃቸው ጌታቸው ዱጉማና አወቀ ጃለታ) ህይወታቸው እንደጠፋ ሰምቻለሁ፡፡ ከዚያ ውጪ ግን ጠላት ሲሸሽ ወደከተማው ገብተው የታፈኑትን ከማስመለቀቅ በቀር የገደሉት ኦሮሞ የለም፡፡"

ወጣቱ ከሚለው በተቃራኒ የመገናኛ ብዙሀን የአማራ ፋኖ አጋምሳን በመቆጣጠር ንጹሀን ኦሮሞዎችን እንደገደለ እየተነገረ እንዳለና በዚህ ላይ ያለው ሀሳብ ምን እንደሆነ ሲጠየቅ፡-

> "ይሄ የተለመደ ማስመሰያቸው ነው፡፡ በተመሳሳይ ኪረሙ ላይ ባለፈው አመት የነሀሴ ሚካኤል እለት 300 የሚደርሱ አማራዎችን ከጨፈጨፉ በኋላ ፋኖ ገደለን ሲሉ ነበረ፡፡ ሲጀመር ፋኖ የሚባል ነገር እዚህ የለም፡፡ ይሄን ስል ፋኖነት የሚያሳፍር ሆኖ ሳይሆን እውነታው እንደዛ ስላልሆነ ነው፡፡ የአማራ ገበሬ ሲመጡ ዝም ብሎ ከሞተ ሸኔ ንጹሀንን ገደለ ይላሉ፡፡ ሊገለው መጥቶ ከተከላከለ ወይም የሸኔን ታጣቂ ከገደለ ደግሞ የአማራ ፋኖ ኦሮሞን ገደለ ይላሉ፡፡ ብቻ ግራ የገባው ነገር ውስጥ ነው ያለነው፡፡ እኛ ገበሬዎች ነን፡፡ በሰላም አርሰን መኖር ነው የምንፈልገው፡፡ ግን አልሆነም፡፡ አትግደሉን ስንል ዝም በሉ እንባላለን፤ እሺ መከላከያ ይምጣና እንዲጠብቀን አድርጉልን ስንል መንግስት ጁንታ በከፈተው ጦርነት ምክንያት ትኩረቱ እዚያ ስለሆነ ታገሱ ይሉናል፤ እራሳችንን ለመከላከል ስንሞክር በኦሮሞ ሀገር ተቀምጣችሁ ሸኔም ቢሆን ኦሮሞ ነው መግደል አትችሉም እንባላለን፡፡ ቢቸግረን የማርያም መንገድ ይሰጠንና ወደ አማራ ክልል እንግባ ብንልም የሚሰማን ጠፋ፡፡"

በአጋምሳ በደረሰው ጥቃት መላኩ ሽፈራው የተባለ የቅርብ ዘመዳቸውን በሞት የተነጠቁ የሀሮ ቀበሌ ነዋሪ በበኩላቸው ፋኖ የሚባለው ነገር ጨርሶ ውሸት እንደሆነ በዚህ መልኩ ይገልጹታል፡-

> "ከሟቹ [መላኩ ሽፈራው] ጋር የአንድ ቅድመአያት ቅርንጫፎች ነን፡፡ በሸኔዎች ተከበናል ድረሱልን ቢል በማግስቱ ከሄዱት ውስጥ አንዱ የእኔ ዘመድ ነው ምንም እንኳን የእኔዎቹን [መላኩ ሽፈራውንና ቤተሰቦቹን] ባያተርፏቸውም፡፡ የእኔ ዘመድ አርሶ የሚበላ ታታሪ ገበሬ እንጂ ፋኖ አይደለም፡፡ ፋኖ የሚባለው እኮ መረረኝ ብሎ ቤቱን ጥሎ ጫካ የገባ ነው፡፡ በርግጥ ከሚደርስብን በደል አንጻር አይደለም ጫካ ሲኦል ያስናፍቃል፡፡ ዋናውን ነገር ስነግርህ የሚጮሁት ለምን ወገኖቻችሁን ስንገላቸው ዝምአትሉም በሚል ነው፡፡"

አባቱን በአጋምሳው ጥቃት እንዳጣ የሚናገረው በ 20ዎቹ የእድሜ ክልል መጨረሻ ላይ የሚገኝ ወጣት በበኩሉ ጥይት ራሱ ገሎ ራሱ ይጮሀል ነው ነገሩ ሲል ይገልጻዋል፡፡

> "ጥይት እራሱ ገሎ እራሱ ይጮሀል ሲባል ሰምተህ ካወቅክ ይሄም እንደዚያው ነው፡፡ የተጨፈጨፈው አማራው ነው፡፡ ገዳይ ደግሞ ኦነግ ሸኔ፣ ቄሮዎች እና አንዳንድ ብሄራቸው ኦሮሞ የሆኑ የአጋምሳ ከተማ ታጣቂዎች ናቸው፡፡ ሰኞ (ነሃሴ 23) ቀን በነበረው ብሄር ተኮር ጥቃት አባቴን የገደሉት የመንግስት ታጣቂዎች ናቸው፡፡ እንደኔው አባት ሁሉ ከ50 በላይ አማራዎች በሸኔና በቄሮዎች በግፍ ተገድለዋል፡፡ ከልቡ እውነቱን ማወቅ የፈለገ ማንኛውም አካል ቦታው ተገኝቶ የሆነውን ማየት ይችላል፡፡"

ሰኞ (ነሃሴ 23) የነበረውን ብሄር ተኮር ግድያና አፈና የሚያቆም የመንግስት አካል በመጥፋቱ በስጋት ውስጥ የነበሩና በአጎራባች ቀበሌ ዘመድ የነበራቸው አማራዎች (እሱን ጨምሮ) የድረሱልን ጥሪ እንዳቀረቡና ይህን ተከትሎ በማግስቱ (ማክሰኞ ነሃሴ 24) ከተለያዩ ቀበሌዎች የተውጣጡ ገበሬዎች ወደ አጋምሳ እንደመጡ የሚናገረው ወጣቱ የኦሮሞ ንጹሀንን ገደሉ የተባለው ግን ከእውነት የራቀ እንደሆነ ይናገራል፡፡

> "ስንታረድ መንግስት ሊደርስልን አልቻለም፡፡ ስለዚህ ድረሱልን ብለን ሁላችንም ለየ ዘመዶቻችን ደወልን፡፡ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) ጠዋት ላይ ከየቀበሌው የተውጣጡ ገበሬዎች መጥተው ከኦነግ ሸኔና እነሱን ደግፈው ሲዋጉ ከነበሩ ታጣቂዎች ጋር በግምት ለ5 ሰአት ገደማ ተዋጉ፡፡ በዚያ መሀል ከእኛም ከእነሱም ብዙ ህይወት ጠፋ፡፡ ቤተሰቡን ሊያድን የመጣው ሀይል ያልቃታል እንጂ እንደማይመለስላቸው ሲያቁ ሸኔዎቹና ጭፍሮቻቸው ሸሹ፡፡ ከዚያ የወገን ሀይል ወደከተማው ዘልቆ ታፍነው የነበሩትንና በየምናምኑ ውስጥ ተደብቀን የነበርነውን ከያለንበት ሰብስበውን ይዘውን ተመለሱ፡፡ እውነቴን ነው የምልህ ለወሬው እንኳን አንድ ሰው አልነኩም፡፡ የሚገርምህ እንደውም አንድ ነሞ አበቡ የሚባል ኦሮሞ ቀደም ብሎ የነበረውን የተኩስ ልውውጥ ሸሽት ከተደበቀበት ሸለቆ ነገር ሲወጣ ይዘውት ምንም ላይ እንደሌለበት አረጋግጠው ወደ ቤቱ እንዲሄድ ነው የለቀቁት፡፡ ፋኖ ገብቶ ኦሮሞዎችን ገደለ የሚሉት ፈጽሞ እውነት የማይመስል ቀልድ ነው፡፡ ሲጀመር ፋኖ የሚባል እኛ ጋር የለም፡፡ ከአማራ ክልል መጣ አይባል መንገዱ ከተዘጋ ስንት

ግዜው፡፡ ሲጀመር መንገዱን መንግስት ቢያስከፍት ስንቱ አማራ ትቶ በወጣ ነበር፡፡ ማን እየታረደ መኖር ይፈልጋል? ልንገርህ የሀሮ ሰው በጨው መብላትና ህክምና ካጣ ሁለት አመት ሊሆነው ነው፡፡ ታፍኖ ወይ አይወጣ ወይ ተንቀሳቅሶ መስራት አልቻለ እየተሰቃየ ነው፡፡ ወላድ እናቶች እየሞቱ ነው፤ ደምግፊትና ስኳር ያለበት እያለቀ ነው፡፡ ታዲያ አማራ ክልል መግባት የሚችልበት መንገድ ቢኖር ምን የሚጠብቅ ይመስልሀል? ብቻ አንድ ቀን ፈጣሪ ከዚህ ግፍ እንደሚያወጣን አምናለሁ፡፡”

በተፈጠረው ነገር ሳቢያ ህይወቱን ያጣ ኦሮሞ ያውቅ እንደሆነ በአማራ ማህበር በአሜሪካ መርማሪዎች የተጠየቀው ወጣቱ የሚከተለውን ብሏል፡፡

“ማክሰኞ (ነሃሴ 24) እለት በነበረው የተኩስ ልውውጥ የተሳተፉ ከኦሮሞውም ከአማራውም ወገን ሞቷል፡፡ ከኦሮሞ የሞተው ግን ሸኔና አብረውት ውጊያ ላይ የተሰለፉት ጭፍራዎቹ ናቸው (በርግጥ ሸኔ የሚባሉት ሲገሉ እንጂ ሲሞቱ ኦሮሞ ናቸው)፡፡ ማወቅ የፈለከው ትክክለኛ ንጹህን ሆነው ህይወታቸው የጠፉ ኦሮሞዎችን ከሆነ ከ 6 ወይም 7 የማይበልጡ በተባራሪ ጥይት እንደሞቱ አውቃለሁ፡፡ ለምሳሌ ሽፈራ ጎቡቴ [እድሜ 55 አካባቢ])፣ አወቀ ጃለታ [65 አካባቢ]እና ጌታቸው ዱጉማ [45 አካባቢ] የሚባሉትን አውቃለሁ፡፡ከዚያ ውጪ ያለው በነበረው ውጊያ የተገደለ ሸኔ ወይም ወዶ ገብ ተፋላሚ ነው፡፡”

## 3.6. የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በኦሮሞ ክልል እየተፈጸመ ባለው አማራ ተኮር የዘር ፍጅት ተባባሪ ከመሆን እንዲታቀብ ስለማሳሰብ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በኦሮሞ ክልል የሚፈጸሙ አማራ ተኮር ጭፍጨፋዎችን በተመለከተ በሚያቀርበው የተዛባ መረጃና በመደበኛነት እየተፈጸሙ ያሉ ብሄር ተኮር ጭፍጨፋዎችን በአግባቡ አጣርቶ፣ መርምሮ፣ ተንትኖ እና በሰነድ አደራጅቶ ከማጋለጥ አንጻር እያሳየው ባለው ከፍተኛ ዳተኝነት በአማራው ላይ በመፈጸም ላይ ለሚገኘው የዘር ማጽዳት ተባባሪ እየሆነ እንደሆነ የአማራ ማህበር በአሜሪካ ያምናል፡፡

ኮሚሽኑ ላለፉት ተከታታይ አመታት በክልሉ እየደረሱ ካሉ መጠነ ሰፊ ብሄር ተኮር ጭፍጨፋዎች አንጻር ተገቢውን ምርመራ አድርጎ ዝርዝር ሪፖረት ከማውጣት ይልቅ የመገናኛ ብዙሀንንና የህዝብን ትኩረት ያገኙ ጥቃቶችን ብቻ እየመረጠ በሁለት ወይም ሶስት ባልበለጡ አንቀጾች መግለጫ ማውጣትን የተለመደ ተግባሩ አድርጎ መቀጠሉ በአማራ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ካለው መጠነ ሰፊ ግድያ፣ የአካልና የአዕምሮ ጉዳት እንዲሁም

እንዲገቡ ከተደረጉበት የአካል ህልውናቸውን የሚደመስስ አስከፊ የኑሮ ሁኔታ አንጻር እጅግ የሚያሳዝን ነው፡፡ የአማራ ማህበር በአሜሪካ በክልሉ እየደረሰ ያለውን መጠነሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በተመለከተ ከሚያደርገው ምርመራ እንደተረዳው ኮሚሽኑ ለሁሉም ጥቃቶች አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥቶ ከመመርመር ይልቅ ከህዝብ ጆሮ የደረሱት ላይ አተኩሮ መግለጫ ማውጣትን መርጧል፡፡ የሚወጡ መግለጫዎችም የደረሰውን የመብት ጥሰት፣ የጥቃቱን ደረጃ፣ የአፈጻጸም ሁኔታዎችን፣ የድርጊቱ ፈጻሚዎችን፣ የመንግስት አካላት ያላቸውን ተሳትፎ እንዲሁም የተጎጂዎችን ዝርዝር ሁኔታ ከማሳየት አንጻር ከፍተኛ ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ በሀገር ውስጥም ሆነ በአለምአቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ በክልሉ ስላለው የሰብአዊ መብት ሁኔታ እውቅና እንዳይኖርና ተገቢውን ትኩረት እዳይሰጠው አድርጎታል፡፡ ከዚህ ባሻገር መግለጫዎቹ በአማርኛ ብቻ የሚዘጋጁ መሆናቸው በራሱ ለጉዳዩ አለም አቀፋዊ ትኩረት እንዳያገኝ አስተዋጾ እያደረገ ይገኛል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በክልሉ የሚፈጸሙ ዘር ተኮር ጥቃቶችን በተመለከተ ኮሚሽኑ የሚያወጣቸው አንዳንድ መግለጫዎች ተጎጂዎችን ለባሰ አደጋ የሚያጋልጡ ብቻ ሳይሆን መሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘቡ እንደሆነና የአማራ ማህበር በአሜሪካ እንደሚያሳስበው ለኮሚሽኑ የገለጸ ሲሆን በተለይም ነሀሴ 12/2013 ዓ.ም በምስራቅ ወለጋ ዞን ኪረሙ ወረዳ የተፈጸመውን ጥቃት በተመለከተ ኮሚሽኑ ያወጣውን ሪፖርት አደገኝነት ድርጅታችን በይፋ ማሳወቁ ይታወቃል፡፡ ይሁንና በኮሚሽኑ በኩል ቀደም ብለው የወጡ የተሳሳቱ መረጃዎችን ለማስተካከልም ሆነ በድጋሚ እንዳይፈጠሩ ለማድረግ እርምጃዎች ባለመወሰዳቸው በዚህ ሪፖርት በስፋት እንደተመለከተው በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን አሙሩ ወረዳ አገምሳ ቀበሌ የደረሰውን ሁኔታ በተመለከተ ኮሚሽኑ ጳጉሜ 1/2014 ዓ.ም ያወጣው መግለጫ የተዛባና ገለልተኝነት የጎደለው ሊሆን ችሏል፡፡ ይህ የኮሚሽኑ ሪፖረት መሬት ላይ ከነበረው እውነት በተጻራሪ ተጎጂዎችን ተጠያቂ የሚያደርግና ነባራዊ ሁኔታውን በአግባቡ ከማስቀመጥ አንጻር በህጸጾች የተሞላ ሆኖ ማህበራችን አግኝቶታል፡፡

የድርጅታችን ምርመራ እንደሚሳየው በጥቃቱ ከ61 በላይ አማሮች በማንነታቸው እንደተገደሉ የሚያሳይ ሲሆን የኮሚሽኑ ሪፖርት ግን የሞቱ አማሮች ቁጥር ሶስት እንደሆነ መግለጽ ብቻ ሳይሆን የሞቱት ሆን ተብሎ በተፈጸመ ብሄር ተኮር ጥቃት ሳይሆን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ታጣቂዎች ''የወረዳው ዋና ከተማ የሆነችውን አቦራ ከተማን ለመያዝ ባደረጉት እንቅስቃሴ'' እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ኮሚሽኑ ባወጣው መግለጫ በአጋምሳ ከተማ ነሀሴ 23 ቀን የተፈጸመው አማራ ተኮር መጠነ ሰፊ አፈና፣ ግድያ፣ ንብረት ማውደም እና ማንገላታት አለመካተቱ ኮሚሽኑ አደረኩት ያለውን ምርመራ ገለልተኝነትና ተገቢነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከአማራ ማህበር በአሜሪካ ምርመራ ውጤት በተጨማሪ የኢትዮጲያ የሰብአዊ መብቶች

ጉባኤ (ኢሰመጉ) ጳጉሜ 4/2014 ዓ.ም ባወጣው ቅድመ ምርመራ ሪፖርት የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በአጋምሳ ከተማ ነሀሴ 23 ቀን ጀምሮ በፈጸመው ብሄር ተኮር ጥቃት በርካቶች መገደላቸውንና በርካቶች መታፈናቸውን ማመልከቱ ኮሚሽኑ አደረኩት ያለውን ምርመራ በድጋሚ እንዲያጤነው የሚያስገድድ ነው፡፡[8] የአማራ ማህበር በአሜሪካ በኮሚሽኑ ሪፖርት ላይ የአጋምሳው የነሀሴ 23 ጭፍጨፋ  አለመካተቱ እንዲሁም ሪፖርቱ ሞቱ ሲል የገለጻቸውን ሶስት አማራዎችንም ቢሆን  በወታደራዊ ኦፐሬሽን ወቅት እንደሞቱ አድርጎ ለማሳየት የተኬደበት ርቀት ከመረጃ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ የተፈጠረ ችግር ነው ብሎ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

ሌላው ሪፖርቱ በነሀሴ 23/2014 ዓ.ም ታጋቾችን ለማስለቀቅ ወደ አጋምሳ ከተማ ከአጎራባች ቀበሌ በመጡ የታጋች ቤተሰቦችና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (ከአጋዦቹ ጋር) መካከል የነበረውን ከ 6 ሰአታት በላይ የቆየ የተኩስ ልውውጥ ምንም ሳይል ያልፍና አጋምሳን ጨምሮ በሌሎች ቀበሌዎች የሚኖሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ያላቸው ነዋሪዎች ላይ ከሀሮ አዲስ ቀበሌ እና ከአማራ ክልል የመጡ ታጣቂዎች ነሃሴ 24 እና 25 ጥቃት እንደፈጸሙና ከ60 በላይ ሰዎች እንደገደሉ ከ70 በላይ የሚሆኑትን እንዳቆሰሉ ይገልጻል፡፡ ይሁንና የድርጅታችን ምርመራ እንደሚያሳየው ከአማራ ክልል የመጣ ምንም ሀይል እንዳልነበረና በብሄሩ ምክንያት የተገደለ ኦሮሞ እንደሌለ ነው፡፡ ነገርግን በአጋምሳ ከተማ ማክሰኞ (ነሃሴ 24) ቀን የታገቱ ቤተሰቦቻቸውን ለማስለቀቅ ከአጎራባች ቀበሌዎች በመጡ የአማራ ተወላጆችና በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (በኦሮሞ ታጣቂዎች በመታገዝ) መካከል በነበረው ከ6 ሰአት በላይ የፈጀ የተኩስ ልውውጥ ከሁለቱም ተፋላሚዎች ብዛት ያላቸው ሰወች ሲገደሉ በተባራሪ ጥይት ምክንያት ደግሞ ከ10 የማይበልጡ ያልታጠቁ ኦሮሞዎች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ የኮሚሽኑ ሪፖርት መሬት ላይ የነበረውን እውነት የማያሳይና ገለልተኝነት የጎደለው በመሆኑ የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ተጨማሪ ምርመራዎችን አድርጎ ማስተካከያ እንዲያደርግና ይቅርታ እንዲጠይቅ የአማራ ማህበር በአሜሪካ ይጠይቃል፡፡

---

[8] የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ‘የሰዎች በህይወትና በሰላም የመኖር መብት ይከበር’ (ጳጉሜ 4/ 2014 ዓ.ም) <https://www.facebook.com/ehrco1/photos/a.2000760023301384/5827726320604716/?type=3&__xts__%5B0%5D=68.ARAPR89CsEVTP9z81uPP0WLjqfAsgEX7QqxcaIu_Q82dc57NUmtcnVIU2QO8N45Xr5H1OCEvnFn7cLBLBxTzR0Uw-8vQm1npQTP_LcM64UOJ6fKYqHV7BEj0RRNmj-XUqhP-ZyXXI6IXfevK112W26ltHv-PAVJY5QkmOy_zAR3igr5RdlL_slEiI-owHvrDs0v2o8wfhWBygSd86TSfMbwxnLxhBDMiaN3OXu_FHQ1khRxLEtxrp8SKT6OaOlYpNNqQUHeZgm6ejp9ZYDnLy0TrlmDZJd0AZEANmjLOVLjK1aLkTkZlyg&__tn__=-R >.

## 4. ማጠቃለያ

ባለፉት ዓመታት በምዕራብ የኦሮሞ ክልል አካባቢዎች በተለይም በሆሮጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምእራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ እና ምእራብ ሸዋ ዞኖች በአማራ ተወላጆች ላይ መጠነሰፊ ብሔር ተኮር ጭፍጨፋዎች ሲፈጸሙ ቆይተዋል። ይህንን በአማራ ሕዝብ ላይ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ባሉ አካላት የጋራ ቅንጅት እየተፈፀመ ያለውን አማራን የማጥፋት ዘመቻ የመገናኛ ብዙሀንና የሰብአዊ መብት ተቋማት መርምረው ባለማጋለጣቸው፣ በአደጋው ልክ ባለማውገዛቸውና አለፍ ሲል ደግሞ ተገቢውን ምርመራ ሳያደርጉ የተዛባ ሪፖርቶችን እያወጡ በመሆናቸው በክልሉ በአማራ ተወላጆች ላይ እየተፈጸመ ያለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ከጊዜ ወደጊዜ ተጠናክሮ እየቀጠለ ይገኛል። በተለይ የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በክልሉ እየተፈፀመ ያለውን አማራ ተኮር እልቂት የኢትዮጵያ ሕዝብና ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ በአግባቡ እንዲገነዘበውና መፍትሄ እንዲፈልግለት የማድረግ ሀላፊነት ቢኖርበትም በተቃራኒው ያለውን ችግር ከመሸፋፈንም አልፎ ተጎጂዎችን ጥፋተኛ የሚያደርጉ የተዛባ መረጃዎችን እያወጣ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የአማራ ማህበር በአሜሪካ ኮሚሽኑ በኦሮሞ ክልል እየተፈጸሙ ያሉ ዘግናኝ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በአግባቡ አጣርቶ፣ መርምሮ፣ ተንትኖ እና በሰነድ አደራጅቶ እንዲያጋልጥ እንዲሁም የመርማሪዎቹን ገለልተኝነት በአግባቡ እንዲፈትሽ ለማሳሰብ ይወዳል፡፡ በተመሳሳይ የመገናኛ ብዙሀንም መሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በሚገባ በመመርመር በክልሉ የሚኖሩ አማራዎች ላይ እየደረሰ ያለውን መጠነ ሰፊ የማጽዳት ዘመቻ በማጋለጥ ሙያዊ ሀላፊነታችሁን እንድትወጡና ከታሪክ ተጠያቂነት እራሳችሁን እንድታድኑ ድርጅታችን ጥሪውን ያደርጋል፡፡ ከምንም በላይ የዘር ጭፍጨፋው የሚፈፀምበት የአማራ ህዝብ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ወይም በየትኛውም የአለም ክፍል ቢኖር ይህ የዘር ጭፍጨፋ በቀጥታ የሚመለከተው በመሆኑ በወለጋ እና በሌሎችም የኦሮሞ ክልል እንዲሁም በመላ አገሪቱ የሚፈፀመውን በመንግስት መዋቅር የሚደገፍ የአማራ ዘር ጭፍጨፋ ለማስቆም የሚቻለውን ሁሉ ትግል እንዲታገል ለመላው የአማራ ህዝብ ጥሪያችንን እናቀርባለን::